The role of teachers' core instructional practices in predicting Amharic reading achievement among early grade students

Tsegaye Girma
Department of Language Education, School of Teacher Education, College of Education, Bahir Dar University

Marew Alemu
Department of Language Education, School of Teacher Education, College of Education, Bahir Dar University.

Selomie Zewdalem
Department of Language Education, School of Teacher Education, College of Education, Bahir Dar University

Abstract

This study examined the influence of teachers' core instructional practices—planning, classroom management, and assessment—on early grade students' reading achievement. Using correlational design, the study involved 160 Grade 2 and Grade 3 students and 8 Amharic language teachers from Ewket Fana, Dilchibo, Shimbit, and Teyima elementary schools in Bahir Dar during the 2025 school year. Data were collected through reading tests, classroom observations, and document analysis, The data were analyzed using bivariate linear regression. The results showed a significant positive association between teachers' instructional practices and students' performance in letter-name identification, reading of familiar and nonsense words, oral reading fluency, and reading comprehension. Planning practice (β = .721–.946, R^2 = .519–.896, $p < .05$), classroom management (β = .718–.794, R^2 = .515–.630, $p < .05$), and assessment practice (β = .714–.828, R^2 = .510–.685, $p < .05$) emerged as significant predictors of reading achievement. However, teachers' planning and assessment practices were not significantly associated with students' phonemic awareness (β = .304–.608, R^2 = .093–.370, $p > .05$). Overall, the findings indicate that, except for phonemic awareness, teachers' core instructional practices substantially predict early grade reading achievement in the Amharic context.

ARTICLE HISTORY
Received: 10 June, 2025
Accepted: 26 December, 2025

KEYWORDS
Instructional planning; Classroom management; Assessment; Reading achievement

መግቢያ

ቋንቋን በመማር ሂደት ትኩረት ተሰጥቷቸው ሊዳብሩ ከሚገባቸው ክሂሎች መካከል የማንበብ ችሎታ በዋናነት ይጠቀሳል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት በማንበብ ችሎታና በአካዳሚያዊ ስኬት መካከል ጠንካራ አዎንታዊ ዝምድና አለ:: Zebron (2022) እና Cardenas (2024) እንዳመለከቱት የማይቋረጥ የማንበብ ተግባር የቃላት ዕውቀትን ያሻሽላል፣ የማስታወስ ችሎታን ያሳድጋል፣ ለነገሮች ትኩረት የመስጠትና በጥልቀት የማሰብ ችሎታን በማሳደግ ሐሳቦችን ከተለያየ አቅጣጫ የመመልከትና

CONTACT Tsegaye Girma tsegayegirma231@gmail.com
© **2026** The Author (s). **Open Access**. This article is licensed under a Creative Commons Attribution 4.0 International License
DOI: https://dx.doi.org/10.4314/bdje.v26i1.4

የመተንተን፣ ከዳህራዊ ግንዛቤ ጋራ የማዋሓድ ችሎታን ያሳድጋል፤ እነዚህ የዳበሩ ችሎታዎች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ስኬት እንዲገኝ ያስችላሉ:: Cox (2024, p.3) በበኩላቸው "የማንበብ ክሂል የመማሪያ መንገድን የሚወስን ነው" በማለት ማንበብ የአካዳሚያዊ ስኬት መግቢያ በር መሆኑን ገልጸዋል:: Cardenas (2024) እንዲሁ፣ አሁን ካለው የዲጂታል ዓለም በቀላሉ ከሚገኙ ዓይነተ-ብዙ የጽሑፍ ዘውጎች መካከል የሚጠቅመውን ብቻ በጥልቀት ገምግሞ በመውሰድ ለስኬት መብቃት የሚቻለው አንብቦ በመረዳት ችሎታ እንደሆነ ያስረዳሉ::

የማንበብ አካዳሚያዊና የእድሜ ልክ መማር ስኬቶች እውን እንዲሆኑ በዋናነት መሠረት በሚጣልበት ደረጃ ለክሂሉ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል:: ይህንን በተመለከተ Hogenboom (2022, p.11) "የልጆች ቀደምት የቋንቋ ልምዶች ለቀጣይ ስኬቶቻቸው መሠረት ነው፤" ሲሉ፣ Kern and Friedman (2009) ደግሞ ቀደምት ስኬት፣ ወደጥሩ አካዳሚያዊና ሥነልቡናዊ አቅጣጫ የሚያመራ አዎንታዊ የሕይወት ዘመን ስኬት ይወስዳል፤ በማለት ይገልጻሉ:: ይህን ሐሳብ Li (2015, p. 2) "ልጅነት በቀላሉ ማንበብ የሚለመድበት ነው" ("Earlier is Easier") ይሉታል:: በአጠቃላይ በመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች ለማንበብ ትኩረት መስጠት የሚከተሉት አምስት ጥቅሞች አሉት፤ (ሀ) ኒዩሮሎጂካል፤ ልጆች ሲያነቡ የአንጎል ሴሎች ድር ይጠነክራል፤ አዳዲስ ድሮች ይፈጠራሉ፤ ይህም አንጎልን በፍጥነት ያዳብራል:: በዚህም በመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች (ልጆችን ከቀጣዮቹ እድሜዎች ይልቅ) በቀላሉ በጣም ፈጣን አንባቢዎች ማድረግ ይቻላል፤ (ለ) አካዳሚያዊ፤ ኒዩሮሎጅካል መዳበሩ ከመነሻው አካዳሚያዊ ስኬት እንዲፈጠር ያደርጋል፤ (ሐ) ሥነልቡናዊ፤ ቀደም ብሎ ማንበብና አካዳሚያዊ ስኬት ያገኙ ልጆች በራስ መተማመን (ግለብቃት እምነት) ይኖራቸዋል፤ (መ) ማኅበራዊ፤ ማኅበራዊ ግንዛቤያቸው ያድጋል፤ ከቢጤዎቻቸው መካከል ያላቸው ማኅበራዊ ደረጃ ከፍ ይላል፤ (ሠ) ቋንቋ ነክ፤ ከጅምሩ የበለጸገ የቃላት፣ የሰዋስው፣ የጽሕፈትና የተግባቦት ዕውቀትና ክሂል ለእድሜ ልክ መማር ወሳኝ ይሆናል (EAES, 2022; Hogenboom, 2022; Kern & Friedman, 2009; Li, 2015):: NRP (2000)፣ Read M&E (2018) እና RTI International (2016) የማንበብን በልጅነት የመማር ጠቀሜታ በተመለከተ ከላይ የቀረቡ ሐሳቦችን ሲያጠናክሩ፣ እድሜ ሲጨምር ማንበብ መማር ከባድ ይሆናል፤ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት በመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች ማንበብ በበቂ ሁኔታ የተማሩ ልጆች ደረጃውን በስኬት የማጠናቀቅ እድላቸው ከፍ ያለ ሲሆን ይህንን ዕድል ያላገኙ ግን ክፍል የመድገምና ትምህርት የማቋረጥ እድላቸው ይጨምራል::

በመጀመሪያዎቹ የክፍል ደረጃዎች ትኩረት ሊደረግባቸው የሚገቡ የማንበብ አላባዎች፤ የንግግር ድምፆች ግንዛቤ (phonemic awareness)፣ ትዕምርተ-ድምጻዊ ግንዛቤ (graphophonemic awareness)፣ አቀላጥፎ ማንበብ (reading fluency)፣ የቃላት ዕውቀት (vocabulary knowledge) እና አንብቦ መረዳት (reading comprehension) ናቸው (NRP, 2000):: Lin (2001) እነዚህ አላባዎች በጀማሪ ክፍሎች፣ መምህራን የሚያተኩሩባቸውና የሚመዝኗቸው፣ ወላጆች የልጆቻቸውን የቋንቋ ችሎታ በተመለከተ የሚጠይቋቸው እንደሆኑ ሲገልጹ፣ RAES (2018, p. 8) በበኩላቸው "አምስት መሠረታዊ የማንበብ አላባዎች" ("the big five of reading") ይሏቸዋል:: እነዚህ አላባዎች ለስኬታማ የማንበብ ሂደት ወሳኝ ናቸው፤ ለእድሜ ልክ መማር ስኬትም ጠንካራ መሠረት ይጥላሉ (Bower, 2017):: አላባዎቹ ጥራት ላለው የመሠረታዊ ማንበብ-መጻፍ ክሂሎች (literacy) ትምህርት ወሳኝ ስለሆኑ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት (በልጅነት ዘመን) ልዩ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል (NRP, 2000)::

የንግግር ድምፆች ግንዛቤ፤ ቃላት በሚነበቡበት/በሚጠሩበት ጊዜ በውስጣቸው ያሉ አነስተኛ ቅንጣቶችን (ድምፆችን) ማዳመጥ፣ ነጥሎ ማመልከትና በድምጸቹ መገልገል (ድምፆችን መነጠል፣ ማጣመር፣ ተመሳሳዮችን ማመልከት፣ መነሻውን፣ መካከለኛውንና መድረሻውን ድምፅ መለየት/መጥራት ወዘተ) መቻል ነው (EAES, 2022; Cox, 2024; George, 2023; Gump, 2024; Read M&E, 2018; RTI International, 2016):: NRP (2000) በ52 የጥናት ውጤቶች ላይ ልዕለ-ትንተና አካሂደው፣ ሕጻናትን የንግግር ድምፅ ግንዛቤ በማስተማር d = 0.53 – 0.86 የተጽዕኖ መጠን (effect size) ያለው ውጤት እንደተገኘና ክሂሉ የማንበብ ችሎታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ሕጻናት ወሳኝ ትምህርት እንደሆነ አመላክተዋል:: ትዕምርተ-ድምጻዊ ግንዛቤ የፊደል-ድምፅ ግንኙነት ነው:: የንግግር ድምፆችን ከጽሑፋዊ ምልክቶቻቸው ወይም ፊደሎች ጋራ አዋሕዶ ማንበብ/መጥራት (decoding) ነው (Cox, 2024; George, 2023; RAES, 2018):: NRP (2000) በ38 ጥናቶች ላይ ልዕለ-ትንተና አድርገው 76% መምህራን ይህንን ክሂል በማስተማራቸው (ክሂሉን ከማይጠቀሙት ይልቅ) ውጤት/ለውጥ እንዳገኙና የተጽዕኖ መጠኑም በጀማሪ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች ላይ ከፍ ያለ መሆኑን (effect size d= 0.44) አመላክተዋል::

አቀላጥፎ ማንበብ፤ አንድን ጽሑፍ በተገቢ ፍጥነት (rate)፣ በትክክል (accuracy) እና በተገቢ አገላለጽ (prosody) ማንበብ መቻል ነው:: አቀላጥፎ የማንበብ የመጨረሻ ግብ አንብቦ መረዳትን እውን ማድረግ ሲሆን፣ ይህ ግብ እንዲሳካ ደግሞ በተደጋጋሚ ልምምድ የተማሪዎች በፍጥነት የማንበብ፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ቃላትን የመጥራት ችሎታ እንዲዳብር ማድረግ ያስፈልጋል (EAES, 2022; Read M&E, 2018; RTI International, 2016):: ክሂሉ ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ ምን ያህል ቃላትን በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማንበብ ቻሉ? የሚለውን ይመለከታል (RAES, 2018):: በኢትዮጵያዊያን ተማሪዎች ላይ በተካሄደ ሀገርአቀፍ ጥናት፣ ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ የሚያነቧቸው ቃላት ቁጥር ሲጨምር አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውም እያደገ እንደሚሄድ ተመላክቷል (Piper, 2010)::

የቃላት ዕውቀት፤ ሐሳብን በመግለጽና ሐሳብን በመቀበል ሂደት ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላትን በትክክል ማንበብና ፍቻቸውን በትክክል መለየት መቻል ነው (EAES, 2022; RAES, 2018; Read M&E, 2018; RTI International, 2016):: Cox (2024) እንደሚሉትም ማንኛውንም አሐድ ለመረዳት የቃል ንበትና ፍቺ ዕውቀት ወሳኝ ነው። የሕጻናት የቃላት ዕውቀት ከፍ ያለ ከሆነ (የአሐዱን 90% ቃላት የሚያውቁ ከሆነ) ንበታቸው ንግግርአከል ይሆናል፤ የቃላቱን ፍቺ በቀላሉ መለየት ይችላሉ፤ የተለያዩ የጽሑፍ ዘውጎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ያድጋል (George, 2023; Goldberg , 2025)።

አንብቦ መረዳት፤ በቃል፣ በዓረፍተነገር፣ በአንቀጽና በሙሉ ጽሑፍ ደረጃ በግልጽና በአመስጥሮ የቀረቡ ጽሑፋዊ ሐሳቦችን መተርጎምንና መጠቀምን ይመለከታል (EAES, 2022; RAES, 2018; Read M&E, 2018; RTI International, 2016;):: Cox (2024) እንደሚሉት ክሂሉ ቀደም ብለው የተገለጹ ክሂሎች ድምር ውጤትና የማንበብ ትምህርት የመጨረሻ ግብ ነው:: ዕውቀትና መረጃዎችን በመለየት፣ በመተንተን፣ በማብላላትና ከዳራዊ ዕውቀት ጋራ አዋሕዶ መረዳትን እውን ለማድረግ ደግሞ አንድምታ የመመሥረት፣ በጥልቀት የማሰብ፣ ጥያቄ የመጠየቅ፣ ዳራን ከጽሑፋዊ አሐዱ መረጃዎች ጋራ የማዛመድና የመሳሰሉ በርካታ ንኡሳን ክሂሎችን ማዳበር ያስፈልጋል (George, 2023)::

A’yunin (2020) እና Untailawan (2020) እንዳመላከቱት አንብቦ በመረዳት ክሂል ላይ ተፅዕኖ አድራሽ ተላውጦዎች በርካታ ሲሆኑ፣ ከእነዚህ መካከል ከተማሪዎች ሁኔታ፣ ለትምህርት ከቀረበው

ውሕድ-አሐድ ባሕርይና ከአካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋራ የተያያዙ ተለውጦዎች ይጠቀሳሉ። Francisco and Celon (2020) እና Karngbeae and Kennedy (2022) ደግሞ የመምህራን የትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ (teachers' instructional practices) ጠንካራ ተፅዕኖ አድራሽ ተለውጦ እንደሆነ ይከራከራሉ:: ጻሕፍቱ አያይዘውም፣ የመምህራን የቅድመዝግጅት፣ የማስተማር ሂደትና፣ ሂደቱንና ውጤቱን የመገምገም ተግባራት በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ወሳኝ ጉዳዮች እንደሆኑ ያስረዳሉ:: የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ እንዲሻሻል ቁልፍ ተግባራቱን (ማቀድ፣ የክፍል አመራር፣ መመዘን) በቅንጅት ማከናወን የግድ እንደሆነ ደግሞ Bibon (2022)፣ Calonia et al. (2023) እና Ullah et al. (2021) ይገልጻሉ::

ቀዳሚው ቁልፍ ተለውጦ ማቀድ ነው፤ ማቀድ ታሳቢ የሚደረገውን ግብ ዒላማ ያደርጋል፤ ግቡ በትምህርቱ ዓላማ ውስጥ በግልጽ ይመላከታል፤ ለዓላማው መሳካት አስፈላጊ ግብዓቶች (የትምህርት ይዘቶች) ይቀርባሉ፣ ግብዓቶችን ለመጠቀም የሚያስችሉ ስልቶች (የመማር ዘዴዎች) እና መርጃ መሣሪያዎች ይለያሉ፤ በሂደቱ ዓላማዎች እየተሳኩ መሆኑን፣ በማጠናቀቂያው ላይ ደግሞ ዓላማዎች መሳካታቸውን መመርመር የሚያስችሉ ምዘናዎች ይሰፍራሉ (Calonia et al., 2023; Saad et al., 2010):: እነዚህን ቅድመ-ዝግጅቶች በትክክል ማከናወን የመማር ማስተማር ሂደቱ በአግባቡ እንዲከናወን ያስችላል (Bibon, 2022):: Farhang et al. (2023) እንደሚያስረዱትም፣ በትክክል የታቀደ ትምህርት ግማሽ እንደተፈጸመ ይቆጠራል፤ ለዚህም ተፈላጊ ተግባራት መካተትና አፈጻጸማቸው መመላከት ይኖርበታል (König et al., 2021)። Enow and Goodwyn (2018) እንዲሁም Lai and Lam (2011) ይህንን ሐሳብ ሲያጠናክሩ፣ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ እንዲዳብር ከተፈለገ እርምጃው ትምህርትን ከማቀድ መጀመር ያስፈልጋል፤ ተግባሩም በዕውቀት መመራትና መፈጸም ይኖርበታል። እቅድ መማር ማስተማርን ይመራል፤ ማንኛውም የማስተማርም ሆነ የመማር እንቅስቃሴ ትኩረት ውጤት ላይ እንዲሆን ያስችላል (Chizhik & Chizhik, 2018; Janssen et al., 2019)::

ትምህርትን በወጉ ማቀድ ብቻውን የግብ ስኬትን አያስገኝም፤ እቅዱ በወጉ በክፍል ውስጥ መተግበር ይኖርበታል፤ በቅድመ-ትምህርት፣ በትምህርቱ ሂደትና ማጠቃለያ ሊከወኑ የሚገባቸው የመማርና የማስተማር ተግባራት በእቅዱ መሠረት መፈጸም ይኖርባቸዋል (Osborne, 2021; Zhu & Kaiser, 2022):: ለዚህ ደግሞ የመማሪያ ክፍሉን በሚገባ ማደራጀትና መምራት ይጠበቃል (Wenglinsky, 2001)። ይህ ሁለተኛ ቁልፍ ተለውጦ (ማደራጀትና መምራት) የመማሪያ ክፍልን በዕውቀት መምራት ተማሪዎች የትምህርቱን ዓላማና ይዘቶች በግልጽ እንዲለዩ፣ ቅድመትምህርት፣ የትምህርት ሂደትና ድኅረትምህርት ተግባራትን በነቃ ተሳትፎ እንዲያከናውኑ፣ ለተግባራቱ የተመደበውን ሰዓት በተገቢው ሁኔታ እንዲጠቀሙ፣ የመምህርን ክትትልና ድጋፍ ተጠቅመው የትምህርቱን ዓላማ እንዲያሳኩ ይረዳል (Adeleke & Akere, 2023; Bas, 2025; Olayvar, 2021; Ozdemir, 2020):: Beaulieu (2023) እንደሚያብራሩት፣ ክፍልን መምራት የታቀደው ይዘት ወደተማሪዎች ግልጽና ሳቢ ሆኖ እንዲደርስና የትምህርቱ ዓላማ እንዲሳካ ምቹ የመማር አካባቢን መፍጠር ነው፤ ይህ ደግሞ የዕለት ተዕለት ትምህርትን የሚፈለግና የሚወደድ ያደርጋል። Chibsa (2024)፣ Farook and Ahmed (2021)፣ Terada (2019) እና Thomas et al. (2010) እንደሚገልጹትም ክፍልን መምራት፣ የትምህርት ግብዓቶችን በሥርዓት በማደራጀት ለመማር ማስተማር ሂደቱ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ፣ የተማሪዎችን ተሳትፎ በማረጋገጥና አላስፈላጊ ባሕርያትን በመቆጣጠር እውን የሚሆን ቁልፍ የማስተማር ተግባር ነው።

ሦስተኛው ቊልፍ ተላውጦ ምዘና ነው:: ምዘና የመማር ማስተማር አካል ነው፤ በትምህርቱ ሂደት ሲተገበር ክፍተቶችን እየለዩ ማስተካከያ ማድረግ ያስችላል፤ በትምህርቱ ማጠናቀቂያ ላይ ሲመጣ ደግሞ የዓላማውን መሳካት/አለመሳካት ያረጋግጣል፤ ቀጣይ የመማር ሂደቶች የበለጠ ውጤታማ እንዲሆኑ መነሻ ይሆናል (Calonia et al., 2023):: Li (2012) እና Ullah et al. (2021) እንደሚገልጹትም፣ ውጤታማ የመማር ሂደት በምዘና ይደገፋል፤ ከምዘና ትምህርት ይገኛል፤ ክፍተት ይለያል፤ ማስተካከያ ብልኃቶች ይመለከታሉ፤ ቀጣዩ የተሻለ ይሆናል። ምዘና እያንዳንዱን የትምህርት ሂደት (መግቢያ፣ ዋና የትምህርት ክፍል፣ ማጠቃለያ) ይመለከታል፤ በእያንዳንዱ ደረጃ የተማሪዎች ክፍተት እየተለየ ድጋፍ ይሰጣል፤ ማስተካከያ ይደረጋል፤ ይህም የዕለቱን ትምህርት ዓላማ በታቀደው ልክ ውጤታማ የመሆን እድል ያሰፋል። ከዚህ በተጨማሪ ምዘና ለስኬትም ሆነ ለውድቀት ተጠያቂነትን ለማስፈንና በተለይም ድክመቶች እንዲስተካከሉ አቅጣጫ ለማመላከት ወሳኝ ጉዳይ ነው (Cai et al., 2022; Xuan et al., 2022):: ከተጠያቂነት ባሻገር ምዘና ውጤታማ ፈጻሚዎችን በማበረታታት ለሌሎች አርኣያ እንዲሆኑ የሚያስችል ዐቢይ የመማር ማስተማር ሂደት አካልም ነው (Yan & Chiu, 2022)::

ውጤታማነቱ በማቀድ፣ በማደራጀትና በመምራት፣ እንዲሁም በመመዘን ተግባራት ጥራት ላይ በሚመሠረተው የማንበብ ችሎታ ላይ ትኩረት ማድረግ፣ እንዲሁም በጀማሪ የክፍል ደረጃዎችና በማንበብ አላባዎች ትምህርትና ምዘና ላይ ማተኮር፣ በምርምርና በተግባር የተፈተኑ ንድፈ-ሐሳባዊና ብልኃታዊ መሠረቶች አሉት:: ከመሠረቶች መካከል በዋናነት ማኅበረ-አእምሯዊ ንድፈ-ሐሳብ (social-cognitive theory) እና ሁሉ-አቀፍ መሠረታዊ ማንበብ-መጻፍ ክሂሎች ትምህርት (comprehensive or Holistic literacy instruction) በመምህራን ቊልፍ የማስተማር ተግባራትና በተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ለሚያተኩረው ለዚህ ጥናቱ መሠረቶች ናቸው:: ትምህርት በግለሰባዊ ባሕርይና ክሂሎች እድገት ላይ ያተኩራል፤ የባሕርይና የክሂሎች እድገት ደግሞ በትምህርት ታሪክ ቀዳሚ ተጠቃሽ በሆነው የአልበርት ባንዱራ ማኅበረአእምሯዊ የመማር ንድፈሐሳብ ላይ ይመሠረታል (Bandura, 1977)። በመማር ሂደት ለአእምሯዊ ግንዛቤ ትኩረት የሚሰጠው ማኅበረአእምሯዊ ንድፈሐሳብ በዋናነት በምልከታ ሚና (ሌሎች የሚሠሩትን በመመልከት/በመኮረጅ መማር)፣ አርኣያ ሆኖ በማሳየት (አርኣያተኮር ትምህርት፣ የሚና ጨዋታና አስመስሎ ማቅረብ) እና የመማር ሂደትን በማጠናከር ላይ ትኩረት ያደርጋል (Widodo & Astti, 2024)። ብቃት ያላቸው አርኣያዎች፣ በመማር ስኬት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፤ አርኣያዎችን ምሳሌ ማድረግና እነሱን በመመልከት መማር "እኔም እችላለሁ!" የሚል ግለብቃት እምነትን ይፈጥራል፤ ግለብቃት እምነታቸው ከፍ ያለ ተማሪዎች ደግሞ ከፍተኛና ጥራት ያለው የትምህርት ውጤት ይሻሉ፤ ከፍተኛ ጥረት በማድረግም ውጤቱን እንደሚያሳኩ ያምናሉ (Yılmaz & Yılmaz, 2019)።

በምልከታና ከአርኣያዎች በመማር ሂደት ልዩ ልዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች (ለምሳሌ፣ ወላጆች፣ መምህራን፣ ቢጤዎች) የተማሪዎችን የማንበብ ተግባር በተመለከተ የሚሰጧቸው አዎንታዊ ምጋቤምላሾች መማርን በማጠናከር ተማሪዎች ለውጤት እንዲበቁ ያስችላሉ (Lim, 2015)። ማኅበራዊ መስተጋብሩ የተማሪዎችን የመማር ተሳትፎ ይጨምራል፤ በትብብራዊ ተራክቦ አማካኝነት የመማር ትጋትን ይፈጥራል፤ ማኅበራዊ ተግባቦትን ያሰድጋል፤ በጋራ የመሥራት፣ ግጭቶችን በራስ የመፍታትና ማኅበራዊ ክሂሎችን የማሳደግ አቅምን ይፈጥራል (Widodo & Astti, 2024):: Yılmaz and Yılmaz (2019) ማኅበራዊና አእምሯዊ ችሎታን በማሳደግ ላይ የሚያተኩረው ማኅበረአእምሯዊ ንድፈሐሳብ የጀማሪ የክፍል ደረጃ ተማሪዎችን ማኅበራዊና ሞራላዊ ስሜት በማሻሻል ረገድ አዎንታዊ ሚና እንዳለው ሲገልጹ፣

Eekhof et al. (2021) ደግሞ የንድፈሐሳቡን ብልኃቶች (በምልከታ መማር፣ አርኣያነትና ትምህርትን ማጠናከር) በመጠቀም የጀማሪ ክፍል ደረጃ ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ማዳበር እንደሚቻል ያስረዳሉ፤ በትክክል ማንበብ፣ በፍጥነት ማንበብ፣ በተገቢ ቅላጼ ማንበብ በብዛት አርኣያዎችን በመመልከት (በማዳመጥ) የሚለመዱ፣ በተደጋጋሚ ጥረት የሚዳብሩ ናቸው።

የማንበብ ችሎታ እንዲዳብር ደግሞ የማንበብ አላባዎችን (የንግግር ድምፅ ግንዛቤን፣ የድምፅና የፊደል ግንኙነት ግንዛቤን፣ አቀላጥፎ ማንበብን፣ የቃላት ዕውቀትንና አንብቦ መረዳትን) በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት ማስተማር (Holistic approach) አስፈላጊ ነው (NRP, 2000):: Castles et al. (2018) እንደሚያስረዱትም ክሂሎቹን በተፈጥሯዊ ቅደምተከተላቸው ከማስተማር ይልቅ አቀናጅቶ ማስተማር ውህድ ዕውቀትና ክሂል እንዲኖር ያስችላል፤ አንብቦ በመረዳት ጊዜ ድምጽን የመለየት፣ ፊደሎችን ከትዕምርቶቻቸው ጋራ የማዛመድ፣ ቃላትን የመለየትና አቀላጥፎ የማንበብ ሂደቶች ይኖራሉ፤ በአቀላጥፎ ማንበብም ጊዜ እንዲሁ ሌሎች አላባዎች ይካተታሉ። ይህ ቅንጅታዊ ሂደት ተማሪዎች የማንበብ አላባዎችን በማዋሃድ ከፍ ያለ አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዲኖራቸው ከማድረጉም በተጨማሪ የተለያየ ዘውግ ያላቸው፣ አዳዲስ ቃሎችን፣ አገላለጾችንና ጽንሰሐሳቦችን ያካተቱ ውሕድአሐዶችን በቀላሉ አንብበው እንዲረዱ ያስችላቸዋል (Rayner et al., 2001)።

ባጠቃላይ ከላይ የተቃኙትን ጠንካራ የንድፈሐሳብ ማሕቀፎችና ሰፊ የምርምር ግኝቶች መሠረት የሚያደርገው ማንበብ፣ መምህራን በሚያከናውኑት የትምህርት ዝግጅትና አቀራረብ ላይ ይመሠረታል:: ማንበብ ውጤታማ እንዲሆን (የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ እንዲሻሻል) ደግሞ የትምህርቱ ዝግጅቶችና አቀራረቦች ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወን ይኖርባቸዋል። ይህ ጥናትም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህራን ትምህርትን የማቀድ፤ ክፍልን የመምራትና የመመዘን ተግባራት በጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ መዳበር ላይ ያለውን አስተዋፆ መርምሯል::

የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ቀደም ሲል እንደተገለጸው፣ በማኅበረአእምሯዊ ንድፈሐሳብና ሁሉአቀፍ መሠረታዊ የማንበብ-መጻፍ ብልኃት፣ መማር የሚከናወነው በዋናነት በምልከታ፣ ከአርኣያዎች ዕውቀትና ክሂል በመቅሰምና የመማር ሂደቱን በማኅበራዊ መስተጋብር በማጠናከር ነው። በዚህ ሂደት የሚቀርቡ አርኣያዎችና የማኅበራዊ መስተጋብር እድሎች የተማሪዎችን ግለብቃት እምነትና ተነሳሽነት በማሳደግ ራስመርና ከፍተኛ ውጤት የሚሹ እንዲሆኑ ያስችላል፤ ይህ እንዲሆን ደግሞ የመማር ማስተማር ሂደቱ ከእቅድ እስከግምገማ ድረስ መስተጋብሮችን በሚያሳልጥና ከአርኣያዎች የመማር እድልን ሊያሰፋ በሚችል መልኩ መቃኘት ይኖርበታል (NRP, 2000; Usher & Schunk, 2018)። እነዚህ መሠረታዊ ሐሳቦች፤ የትምህርት እቅድ፣ የክፍል ውስጥ ተግባራትና የግብ ስኬት ማረጋገጫ ምዘናዎችን ውጤታማነት በየጊዜው የመፈተሽና ማስተካከያ የማድረግ አስፈላጊነትን ያመላክታሉ፤ ይህም ለዚህ ጥናት መነሻ ሆኗል።

በኢትዮጵያ በ2010 ሁለት የከተማ አስተዳደሮችን ጨምሮ በስምንት ክልሎች በስድስት የአፍ መፍቻ ቋንቋዎች፣ እንዲሁም በ2014 በሁለት ተጨማሪ ቋንቋዎች (ሀዲይሳና ወላይታቶ) የጀማሪ ተማሪዎች የማንበብ ምዘና (EGRA) ጥናት ተካሂዷል (Piper, 2010; RTI International, 2016):: በጥናቱ የተገኘው ውጤት የልጆች የማንበብ ችሎታ እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አመላክቷል:: በ2ኛና በ3ኛ ክፍሎች ደረጃ የማንበብ ምዘናው ያተኮረባቸው የጀማሪ ተማሪዎች ቁልፍ የማንበብ አላባዎች፤

የንግግር ድምፆች ግንዛቤ (የቃላትን ድምፆች መለየት)፣ የፊደል ስያሜ ዕውቀት፣ ተዘውታሪ ቃላትንና ትርጉምየለሽ ቃላትን ማንበብ፣ አቀላጥፎ ማንበብ (ቃላዊ)፣ አንብቦ መረዳትና አዳምጦ መረዳት ናቸው (Piper, 2010; RTI International, 2016):: ከእነዚህ ምዘናዎች የተገኙ ውጤቶች እንዳመለከቱት የ2ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁት ተማሪዎች መካከል 34% አንድ ቃል እንኳ ማንበብ አልቻሉም፤ 48% አንብቦ በመረዳት ምዘና ምንም ውጤት አላስመዘገቡም። የ3ኛ ክፍል ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ተማሪዎች መካከልም እንዲሁ 20% የሚሆኑት ምንም ቃል ማንበብ አልቻሉም፤ 30% ያህሉ አንብቦ በመረዳት ምንም ውጤት አላስመዘገቡም። ይህም ውጤት በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በትምህርት ሚኒስቴር ከተቀመጡት ዝቅተኛ ተፈላጊ ችሎታዎች (≥ 50) በከፍተኛ ደረጃ ያነሰ ነው:: በብዙዎቹ ክልሎች ከ50% በላይ የሚሆኑት ተማሪዎች አንድም አንብቦ የመረዳት ጥያቄ አልመለሱም (Piper, 2010; RTI International, 2016):: ይህ ውጤትም በኢትዮጵያ በብሔራዊ ደረጃ የማንበብ ትምህርትን ብሎም የተማሪዎችን የማንበብ ክሂል እንደገና መመርመርና ለአፍ መፍቻ ቋንቋ የማንበብ ትምህርት የቅድሚያ ቅድሚያ ትኩረት እንዲሰጥ ገፊ ምክንያት ነበር::

ማንበብን ጨምሮ በቊልፍ የትምህርት ዓይነቶች በተካሄደው ዐራተኛው ብሔራዊ የመማር ምዘና ጥናት (NEAEA, 2013)፣ የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ውጤት ከጀማሪ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ምዘና ውጤት ጋራ የሚደጋገፍ ሆኗል:: ከመሠረታዊ በታች (<50 ውጤት ያስመዘገቡ)፣ መሠረታዊ (50 – 70 ውጤት ያስመዘገቡ) እና ውጤታማ (>70 ውጤት ያስመዘገቡ) በሚሉ ሦስት የማንበብ ችሎታ ርከኖች በተካሄደው በዚህ ምዘና ከግማሽ በላይ የሚሆኑት (54.20%) የ4ኛ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ከመሠረታዊ በታች መሆኑ ተመላክቷል:: በምዘናው መሠረት በውጤታማ የማንበብ ችሎታ ርከን መካተት የቻሉት ተማሪዎች 19.50% ሲሆኑ፣ በመሠረታዊ የማንበብ ችሎታ ርከን ደግሞ 26.30% ተማሪዎች ናቸው::

በ2010 በተካሄደው የጀማሪ ክፍል ተማሪዎች ምዘና (EGRA) የተገኙ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታ ውጤቶችም ከላይ ከቀረቡ ውጤቶች ጋራ ተደጋጋፊነት አላቸው (Piper, 2010)። በ2010 በተደረጉ የአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታ ምዘናዎች የ2ኛና የ3ኛ ክፍሎች ተማሪዎች ውጤት አጥጋቢ አልሆነም። በምዘናው የተሳተፉ ተማሪዎች ፊደላትን የመለየት ችሎታ በ2ኛ ክፍል በደቂቃ 41.4፣ በ3ኛ ክፍል ደግሞ በደቂቃ 54.2 ሆኗል፤ ይህም ከሚጠበቀው ውጤት (≥60) በእጅጉ ያነሰ ነው። ተዘውታሪ ቃላትን በትክክል በማንበብ ረገድ ደግሞ የሚጠበቀው ዝቅተኛ ውጤት ≥50 ሲሆን የተገኘው ውጤት ግን ከዚህ ያነሰ ሆኗል (የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች አማካይ ውጤት በደቂቃ 20 ቃላት፣ የ3ኛ ክፍል በደቂቃ 29.4 ቃላት ነው)። ትርጉምአልባ ቃላትን በትክክል ማንበብ የቻሉት የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማካይ 12.8 ሲሆኑ፣ በ3ኛ ክፍል በአማካይ 18.3 ብቻ ናቸው። አቀላጥፎ ማንበብን በተመለከተም የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ በትክክል ማንበብ የቻሉት 19.1 ቃላትን ብቻ ነው፤ የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ደግሞ 27.9 ቃላትን በደቂቃ በትክክል ማንበብ ችለዋል። አንብቦ ከመረዳት አንጻርም የተገኘው ውጤት በመቶኛ ሲገለጽ የ2ኛ ክፍል ተማሪዎች 22.0% ሲሆን፣ የ3ኛ ክፍል 35.3% ነው፤ ውጤቱ በክፍል ደረጃው ከሚጠበቀው (≥50) ያነሰ ነው። በዚሁ ምዘና ከተሳተፉ ተማሪዎች መካከል ከ2ኛ ክፍል 25%፣ ከ3ኛ ክፍል ደግሞ 20% ያህሉ በቀረበላቸው አሐድ (ታሪክ) ውስጥ ያሉ ቃላትን (ትርጉምአልባ ቃላትን ጨምሮ) በትክክል ለይተው ማንበብ አልቻሉም። አንብቦ ከመረዳት አንጻርም ግማሽ ያህሉ (49.0%) የ2ኛ ክፍል ተማሪዎችና 30.4% የሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ምንም ውጤት አላስመዘገቡም (Piper, 2010)::

በጀማሪ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተካሄደው በዚህ የማንበብ ችሎታ ምዘና ጥናት የተመዘገቡ ዝቅተኛ የማንበብ ችሎታ ውጤቶች በእነዚህ ደረጃዎች (በጀማሪ ክፍሎች) ለማንበብ ክሂል ልዩ ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ያመላከቱ ናቸው። በዚህ የ2010 ጥናት መነሻነትም በኢትዮጵያ በብሔራዊ ደረጃ ለአፍመፍቻ ቋንቋ የማንበብ ትምህርት መሻሻል ቀዳሚ ትኩረት እንዲሰጥ ተደርጓል። ይህንንም ተከትሎ የችግሮቹን ምክንያቶችና መፍትሔዎች በጥልቀት ለመመርምር በርካታ ሀገርአቀፍ ምክክሮች ተደርገዋል፡፡ ምክክሮችንም መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ የማንበብ እድገት ቴክኒካል ድጋፍ ሰጭ ድርጅት (READ TA) እና የአሜሪካ የልማት ተራድኦ ድርጅት (USAID) ከትምህርት ሚኒስቴር ጋራ በመተባበር፣ በሀገርአቀፍ ደረጃ በጥናት ላይ የተመሠረቱ የአፍመፍቻ ቋንቋ የማንበብ መርሐትምህርቶች፣ እንዲሁም የመምህርና የተማሪ መጻሕፍት ተዘጋጅተው ከ2006 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ ውለዋል (NEAEA, 2013)።

ይሁን እንጂ የሥርዓተትምህርት ቀረጻና ትግበራ ከተከናወነ በኋላ የተገኙ ውጤቶችን ለመፈተሽ በተካሄዱ ተከታታይ የጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ምዘናዎች የተገኙ ውጤቶች መሻሻሎች እንዳልታዩ አመላክተዋል:: ለምሳሌ፣ በ2018 በተካሄደው የማንበብ ችሎታ ምዘና በቃላዊ አቀላጥፎ ማንበብ 15.2% የ2ኛ ክፍልና 7.3% የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ዜሮ አንባቢዎች ሆነዋል:: ባጠቃላይ በክፍል ደረጃዎቹ የሚጠበቀውን የብቁ አንባቢነት ደረጃ አሟልተው የተገኙት 4% የ2ኛ ክፍልና 8% የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች ብቻ ናቸው (READ M&E, 2018):: በ2021 በተካሄደው ምዘና ደግሞ ከቀደሙት የማንበብ ምዘናዎች ያነሰ ውጤት ተመዝግቧል:: 59.1% ያህል ተማሪዎች አቀላጥፎ በማንበብ ምዘና ዜሮ አንባቢ ሆነዋል:: ፊደላትን ለይቶ በማንበብ 2ኛ ክፍል 23%፣ 3ኛ ክፍል 23%፣ ተዘውታሪ ቃላትን በማንበብ ከ2ኛ ክፍል 65%፣ ከ3ኛ ክፍል 49%፣ ትርጉምአልባ ቃላትን በማንበብ ከ2ኛ ክፍል 70%፣ ከ3ኛ ክፍል 54%፣ እንዲሁም አቀላጥፎ በማንበብ ከ2ኛ ክፍል 68%፣ ከ3ኛ ክፍል 51%፣ያህል ተማሪዎች ዜሮ አንባቢዎች ሆነዋል ወይም ምንም ውጤት አላስመዘገቡም (EAES, 2022)::

ከ2010 – 2021 የተካሄዱ ምዘናዎች የጀማሪ ክፍል ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ዝቅተኛ መሆኑንና ችግሩን ለመቅረፍ የተደረጉ የሥርዓተትምህርት ቀረጻና ትግበራ ጥረቶች ውጤት አለማስገኘታቸውን፣ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ውጤትም እያሽቆለቆለ መምጣቱን ያመላከቱ ናቸው። ይህም ዋና ዋና ተጽእኖ አድራሽ መንስኤዎችን በምርምር በመለየት የመፍትሔ ሐሳቦችን የማመላከት አስፈላጊነትን የሚያረጋግጥ ነው።

ይህ ጥናትም የመምህራን ቊልፍ የማስተማር ተግባራት (ማቀድ፣ የክፍል አመራርና መመዘን) በተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ያላቸውን አስተዋፆ መርምሯል። የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎችም የሚከተሉት ናቸው፤

1. የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር ከጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ የማንበብ ችሎታ ጋራ ግንኙነት አለውን?
2. የመምህራን የክፍል አመራር ከጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ የማንበብ ችሎታ ጋራ ተዛምዶ አለውን?
3. የመምህራን የክፍል ውስጥ የምዘና ተግባር ከጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ የማንበብ ችሎታ ጋራ ግንኙነት አለውን?

የአጠናን ዘዴ

የጥናቱ ዓላማ የመምህራን ቍልፍ የማስተማር ተግባራት (ማቀድ፣ የክፍል አመራር፣ መመዘን) የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋፆ መመርመር ነው:: ለዚህም ተዛምዷዊ የጥናት ንድፍና ተግባራዊ ተደርጓል። የተማሪዎችን ወቅታዊ ችሎታ መግለጽ የሚያስችል በመሆኑ፤ በተላውጦዎች መካከል ያለውን ዝምድና ማመላከትና ተንባዪ ተላውጦ ተተንባዩን ተላውጦ (output variable) በምን ያህል ደረጃ መግለጽ/መተንበይ እንደቻለ መፈተሽ የሚያስችል በመሆኑ ንድፉ ተመርጧል (Ma & Zhao, 2025)።

ጥናቱ በባሕር ዳር ከተማ በሚገኙና በዓላማተኮር ንሞና በተመረጡ አራት ትምህርትቤቶች (ዕውቀት ፋና፣ ድል ችቦ፣ ጠይማና ሽምብጥ) ተካሂዷል:: መረጃዎችን በበቂ መጠን ማግኘት የሚያስችሉና ከመገኛ ቦታ አንጻር ወካይ ሊሆኑ እንደሚችሉ በመታመኑ ትምህርትቤቶቹ ተመርጠዋል:: ከእያንዳንዱ ትምህርትቤት ከ2ኛና ከ3ኛ የክፍል ደረጃዎች አንዳንድ ክፍሎች (ከ2ኛ 1፣ ከ3ኛ 1) በዕጣ ከተለዩ በኋላ ከጠቃላይ 560 ተማሪዎች መካከል ከየክፍሎቹ 20 ተማሪዎች፣ በድምሩ 160 (ከ2ኛ ክፍል 80፣ ከ3ኛ ክፍል 80) ተማሪዎች በሥርዓት በተዘጋጀ ናሙና (Systematic Sampling) ከተማሪዎች የስም ዝርዝር ከአራት አንድ በመውሰድ በምዘና ተሳትፈዋል። ከእነዚህም መካከል የወንዶቹ ቍጥር 77 (2ኛ ክፍል 36፣ 3ኛ ክፍል 41) የሴቶች ደግሞ 83 (2ኛ ክፍል 44፤ 3ኛ ክፍል 39) ነው:: ከተማሪዎች በተጨማሪ ወንድ 1፣ ሴት 7፣ ባጠቃላይ 8 የጀማሪ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን (ከእያንዳንዱ ትምህርትቤት 2) በጠቅላይ ንሞና ተመርጠው በሚያስተምሩበት ክፍል ለ16 ክፍለጊዜ በክፍል አደረጃጀትና አመራር እንዲሁም በምዘና አፈጻጸማቸው ላይ ያተኮረ በማመሳከሪያ ቅፅ የታገዘ ምልከታ ተደርጓል::

የ2ኛና የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ መሠረታዊ የማንበብ ችሎታ መረጃዎች በሰዓት ገደብ (timed) ምዘናዎች (የፊደል ስያሜ ዕውቀት፣ የተዘውታሪና የትርጉምአልባ/የፈጠራ ቃላት ቃላዊ ንባብና አቀላጥፎ የማንበብ ምዘናዎች) እንዲሁም የሰዓት ገደብ በሌለባቸው (untimed) ምዘናዎች (የንግግር ድምፆች ግንዛቤና አንብቦ የመረዳት ምዘናዎች) ተሰብስበዋል።

የፊደል ስያሜ ዕውቀት መመዘኛው ከ2010 የጀማሪ ክፍሎች የማንበብ ምዘና በቀጥታ የተወሰደ ነው። መመዘኛው 100 የአማርኛ ቋንቋ ፊደሎችን ይዟል:: ይህ መመዘኛ ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ ምን ያህል ፊደላትን በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማንበብ እንደሚችሉ (Letters Correct Per Minute/LCPM) መረጃ መሰብሰብ የሚያስችል ሲሆን ባጠቃላይ 100 ነጥቦች አሉት (እያንዳንዱ ፊደል አንድ ውጤት አለው)። የተዘውታሪና ትርጉም የሌላቸው/የፈጠራ ቃላት የማንበብ ምዘናዎች በሰዓት የተገደቡ (WCPM) ሲሆኑ፣ ከEGRA የ2010 ጥናት በቀጥታ የተወሰዱ ናቸው (Piper, 2010)። ምዘናው ተመዛኝ ተማሪዎች በአንድ ደቂቃ ምን ያህል ቃላትን በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ ማንበብ እንደሚችሉ መረጃ የመሰብሰብ ዓላማ ያለው ሲሆን፣ በተዘውታሪና በፈጠራ ቃላት ምዘና በእያንዳንዳቸው 50 ቃላት ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ ቃል አንድ ነጥብ አለው።

አቀላጥፎ የማንበብ ምዘና ተማሪዎች በአንድ ውሕድአሐድ ካሉ ቃላት በአንድ ደቂቃ ምን ያህሉን በትክክል፣ በፍጥነትና በተገቢ አገላለጽ ማንበብ እንደሚችሉ መረጃ የሚሰበሰብበት ሲሆን፣ ይህም ከEGRA የ2010 ጥናት በቀጥታ የተወሰደ ነው (Piper, 2010)። ምዘናው በትረካዊ አሐድ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ አሐዱ በውስጡ 60 ቃላት አሉት። በምዘናው ለተመዛኞች ከ60 ነጥብ ይመዘገባል (ለእያንዳንዱ ቃል 1)። ሌላው ከEGRA የ2010 የምዘና ጥናት በቀጥታ ተወስዶ ተግባራዊ የተደረገው የማንበብ ችሎታ መለኪያ (አንብቦ የመረዳት) ምዘና ነው (Piper, 2010):: አንብቦ የመረዳት ምዘናው

የሰዓት ገደብ ምዘና አይደለም (በሰዓት ገደብ አይለካም)። ይህ ምዘና አቀላጥፎ ለማንበብ ምዘና በቀረበው ባለ60 ቃላት አጭር ትረካዊ ውሕድአሐድ ላይ የተመሠረተ ሲሆን፣ 5 ጥያቄዎች (5 ነጥብ ያለው) አሉት። ተማሪዎች አቀላጥፈው ካነበቡ በኋላ ባነበቡት ታሪክ መሠረት ለጥያቄዎቹ ምላሽ ይሰጣሉ። የሰዓት ገደብ ከሌለባቸው የማንበብ ምዘናዎች ሌላው፣ የንግግር ድምፆች ግንዛቤ (phonemic awareness) ምዘና ነው። የዚህ ምዘና ዓላማ የተማሪዎችን የንግግር ድምፅ ግንዛቤ/ችሎታ ለመለካት ነው። በምዘናው ከEGRA የ2010 ጥናት በቀጥታ የተወሰዱ 10 ቃላት አሉ (Piper, 2010)፤ ተማሪዎች ቃሎቹ በመዛኝ ሲነበቡላቸው በቃሎቹ ውስጥ ያሉ ድምፆችን ነጥለው ወይም ለይተው ይናገራሉ። ለእያንዳንዱ ቃል 1 ነጥብ ይመዘገባል (ምዘናው በጠቅላላ 10 ነጥብ አለው)።

ሌላው የመረጃ መሰብሰቢያ የሰነድ ፍተሻ ነው። ዓላማውም መምህራን ያዘጋጇቸው ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ሥነትምህርታዊ የእቅድ ዝግጅት መርሖዎችን ማሟላታቸውንና አስፈላጊ ነጥቦችን ማካተታቸውን በተመለከተ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ነው:: ፍተሻው 30 ነጥቦች ባሉት የማመሳከሪያ ቅፅ የተከናወነ ሲሆን፣ የ30ዎቹን ነጥቦች አፈጻጸም በሚገልጹ አራት የደረጃ መወሰኛ ስኬሎች (*በጣም አጥጋቢ* [4]፣ *አጥጋቢ* [3]፣ *አጥጋቢ ያልሆነ* [2]፣ *በጣም አጥጋቢ ያልሆነ* [1]) አማካኝነት ውጤት በመስጠት መረጃዎች ተሰብስበዋል:: የፍተሻ ዝርዝር ነጥቦች ከAhmed (2022)፣ ከEchevarría et al. (2017) እና ከPalad (2025) ሥራዎች በማስማማት የተወሰዱ ናቸው:: በማመሳከሪያ ቅጹም ባጠቃላይ 16 ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች (ከእያንዳንዱ/ዷ መምህር 2) ላይ ፍተሻ ተካሂዷል።

በምልከታዎች የመምህራንን የክፍል አመራር ሂደትና የክፍል ውስጥ የተማሪ ምዘና አፈጻጸምን የተመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል:: የክፍል አመራርና አደረጃጀት አፈጻጸምን የተመለከቱ መረጃዎች ከBeaulieu (2023) እና Terada (2019) ሥራዎች ተስማምተው የተወሰዱ 20 የትኩረት ነጥቦችና አራት የመወሰኛ ደረጃዎች/ስኬሎች (*በጣም አጥጋቢ* [4]፣ *አጥጋቢ* [3]፣ *አጥጋቢ ያልሆነ* [2]፣ *በጣም አጥጋቢ ያልሆነ* [1]) ባሉት የምልከታ ማመሳከሪያ ቅፅ በመታገዝ ተሰብስበዋል። የተማሪ ምዘና አፈጻጸምን የተመለከቱ መረጃዎች ደግሞ ከAhmed (2022)፣ ከEchevarría et al. (2017) እና ከPalad (2025) ሥራዎች ተስማምተው በተወሰዱ 25 ነጥቦችን በያዘ ማመሳከሪያ ቅፅ ተሰብስበዋል። ማመሳከሪያ ቅጹ 4 የደረጃ መወሰኛ ስኬሎች *(በጣም አጥጋቢ* [4]፣ *አጥጋቢ* [3]፣ *አጥጋቢ ያልሆነ* [2]፣ *በጣም አጥጋቢ ያልሆነ*[1]) አሉት። በዚህም ባጠቃላይ ለ16 ክፍለጊዜ ያህል ምልከታ ተከናውኖ የክፍል አመራርና የምዘና አፈጻጸሞችን የተመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል።

የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎች ከተዘጋጁ በኋላ በሦስት የሥነትምህርትና በሦስት የቋንቋ የዩኒቨርሲቲ ተመራማሪዎችንና መምህራንን ባሳተፈ ፓናልና ለመዛኝ ባለሙያዎች በተዘጋጀ ዐውደጥናት እንዲገመገሙ ተደርገው በዋናነት በምዘናዎች አቀራረብ ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ዋናዎቹ መረጃዎች ከመሰብሰባቸው በፊትም ከጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ውጭ የሆኑ የዕውቀት ፋና ትምህርትቤት 10 ተማሪዎችን (ከ2ኛ ክፍል 5፣ ከ3ኛ ክፍል 5) መሠረታዊ የማንበብ ችሎታዎችን በቀጥታ በመመዘን በተገኙ ተመክሮዎችና ግብዓቶች መሠረት በተለይም በሰዓት ገደብ ምዘናዎች የደቂቃ አመዘጋገብና ውጤት አሰጣጥ ላይ ማሻሻያዎች ተደርገዋል።

የትክክለኛነት ፍተሻዎች ከተከናወኑ በኋላ 160ዎቹ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች እንዲመዘኑ ተደርገው የተገኙ የምዘና መረጃዎች አስተማማኝነት (reliability) በክሮንባኽ አልፋ (KR20) ተሰልቶ በሁሉም ምዘናዎች ተቀባይነት ያለው ውጤት ($\alpha > .7$) ተገኝቷል። የፈተናዎቹ፣ የምልከታውና የቃለመጠይቁ የጥያቄ-ውጤት ተዛምዶ (Inter-Item Correlation) በተጨማሪነት ተሰልቶ በእያንዳንዱ

መረጃ መሰብሰቢያ ውስጥ ያለ የእያንዳንዱ ጥያቄ/ነጥብ ውጤት ከሌሎች ጥያቄዎች (ከጠቅላላው ውጤት) ጋራ የጠበቀ ትስስር እንዳለውና በቅንጅት ታላሚውን ችሎታ/ተግባር መመዘን እንደቻለ የሚያረጋግጥ ውጤት (*r*= 0.2 – 0.5) ተገኝቷል።

የዚህ ጥናት ትግበራ የተጀመረው የጥናት መሪ እቅድ (proposal) በማዘጋጀት ነው:: በመቀጠል የመረጃ መሰብሰቢያ መሣሪያዎችን በማዘጋጀት ከባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽሕፈትቤት ኃላፊዎችና ኤክስፐርቶች ጋራ ውይይት ተደርጓል፤ ጥናቱን ለማከናወንም ይሁንታ ተገኝቷል:: ከዚያም የምክክር ዐውደጥናት በማሰናዳት የትምህርት ጽሕፈትቤት ባለሙዎች፣ ርእሰመምህራንና ምክትሎች፣ የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችና ተመራማሪዎች በተሳተፉበት ስለጥናቱ ዓላማዎችና ከእነሱ ስለሚጠበቁ ኃላፊነቶች በማስረዳት ሊደረግ በሚገባው ትብብር ላይ መግባባት ላይ ተደርሷል:: ከዐውደጥናቱ በኋላ ለመረጃ ሰብሳቢዎች ሥልጠና ተሰጥቷል፤ ከሥልጠናው በኋላ በዕውቀት ፋና ትምህርትቤት 10 ያህል የ2ኛና የ3ኛ ክፍል ተማሪዎችን መዝነዋል:: በምዘናው ሂደት ላይ በተደረገው ምልከታና በተመዘገቡት የምዘና ውጤቶች ትንተናም በመዛኞች መካከል የአተገባበር ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል::

በዚህ መልኩ ሁኔታዎች ከተመቻቹ በኋላ በዐራቱ ትምህርትቤቶች በአካል በመገኘት ከመጋቢት 18–24 ፣ 2017 ዓ.ም. በማንበብ ችሎታ ምዘናዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል:: ተማሪዎች በጀማሪ ክፍሎች ምዘና መተግበሪያ መርሖዎችና መመሪያዎች መሠረት፣ ስለምዘናው ዓላማና የትኩረት ነጥቦች ከተገለጸላቸውና በምዘናው ለመሳተፍ ይሁንታ መስጠታቸው ከተረጋገጠ በኋላ በተናጠል ተመዝነዋል:: በመቀጠልም አስቀድሞ በተዘጋጀ የክፍል አመራርና የምዘና አፈጻጸም የማመሳከሪያ ቅፅ በመመራት ከመጋቢት 25–30፣ 2017 ዓ.ም. በእያንዳንዱ ትምህርትቤት የ4 ክፍለ ጊዜ ምልከታ ተደርጓል። ምልከታው ከ1– 3ኛ ክፍሎች የተከናወነ ሲሆን ምልከታ በተከናወነበት ክፍለጊዜ መምህራኑ ያዘጋጁቸውንና የተገበሯቸውን ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች ፎቶግራፍ በማንሳት በሰነድ ፍተሻ ማመሳከሪያ ቅፁ አማካኝነት ምርመራ ተከናውኖባቸዋል::

በሰዓት በሚለኩና የሰዓት ገደብ በሌለባቸው ምዘናዎች የተገኙ መረጃዎች በጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና ስልት (Bivariate Linear Regression) ተተንትነዋል። የሰዓት ገደብ ምዘናዎች በአንድ ደቂቃ፣ በፍጥነት፣ በትክክልና በተገቢ አገላለጽ የተነበቡ ፊደሎች/ቃላት በሚል ተሰልተዋል:: የሰዓት ገደብ የሌለባቸው ምዘናዎች ደግሞ ከቀረቡ ጥያቄዎች በትክክል የተመለሱ ጥያቄዎችን ብዛት በመውሰድ ትንተና ተካሂዶባቸዋል::

በዚህም የመምህራን የማስተማር ዝግጅትና አቀራረብ (ማቀድ፣ የክፍል አመራር፣ መመዘን) ለተማሪዎች የፊደል ስያሜ ዕውቀት፣ የተዘውታሪና ትርጉምአልባ/የፈጠራ ቃላት ንባብ፣ አቀላጥፎ የማንበብ፣ የንግግር ድምፆች ግንዘቤና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ያለው ሚና በተመረጠው የመተንተኛ ስልት (በድኅረት ትንተና ስልት) ተመርምሯል:: በምርመራው የመምህራን የማቀድ፣ የክፍል አመራርና የመመዘን ተግባራት አፈጻጸም እያንዳንዱን የማንበብ አላባ ለማሳደግ ያለው አስተዋፆ ሲሰላ የተተነተኑት ቊልፍ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው:: (ሀ) የመምህራን የማቀድ፣ የክፍል አመራርና የመመዘን ተግባራት ከተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ጋራ ያላቸው ተዛምዶ *(r)* ተሰልቷል፤ (ለ) ተንባዩ ተላውጦ ተተንባይ ተላውጦውን በምን ያህል ደረጃ መግለጽ/መተንበይ እንደቻለ ምርመራ ተከናውኗል:: ይህም ተንባዩ ተላውጦ (ማቀድ፣ የክፍል አመራር ወይም መመዘን) በአንድ መደበኛ ልይይት (standard deviation) ሲያድግ ተተንባዩ ተላውጦ (የተማሪዎች ስድስቱ የማንበብ ችሎታዎች በተናጠል) ምን ያህል የመደበኛ ልይይት ለውጥ አሳዩ? በሚለው የመደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ *(β)* ተተንትኗል:: በተጨማሪም በተጋርቶ

መጠን "R^2" ስሌት የተተንባዩ ተላውጦ ምን ያህል ልይይት (variation) በተንባዩ ተላውጦ ተገለጸ የሚለው በመቶኛ ተሰልቷል:: የተዛምዶው ትክክል የመሆን/የጐልህነት ደረጃም (sig.) በትንተናው ተካትቷል::

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በጥናቱ የተሰበሰቡ መረጃዎች የተተነተኑት በድኅረት ትንተና ስልት ነው። የትንተና ስልቱ ተግባራዊ የተደረገው ደግሞ በቅድሚያ ዋና ዋና እሙኖች (assumptions) መሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላ ነው:: በመጀመሪያ የተፈተሸው የስርጭት ወጥነት (normality) ሲሆን የተሰበሰቡ መረጃዎች በአምድ ግራፍ (histogram) ተሰልተው እሙኑ መሟላቱ ተረጋግጧል። ቀጥሎ መረጃዎች ፈርጀብዙ ተዛምዶ (Multicollinearity) ያላቸው መሆኑ በልይይት ግሽበት ፋክተር (variance inflation factor/VIF)፣ የ"tolerance value" ደግሞ በንጥል ድኅረት ትንተና ስልት (linear regression analysis) ተሰልቶ የተገኘው ውጤት (VIF < 10; toleranec ≥ 1) እሙኑ መሟላቱን አመላክቷል፤ የ"condition index value" < 15 መሆኑም ለእሙኑ መሟላት ተጨማሪ ማስረጃ ሆኗል። ከስርጭት ወጥነትና ከፈርጀብዙ ተዛምዶ ምርመራ በኋላ በመረጃዎቹ ተናጠላዊ አፈንጋጭ ነጥቦች (univariate outliers) አለመኖራቸው በክፋይ ሳጥን (boxplot)፣ የፈርጀብዙ ተላውጦ አፈንጋጭ ነጥቦች (Multivariate outilers) የሌሉ መሆኑ በማሀላኖቢስ የልዩነት መወሰኛ (Mahalanobis distance)፣ Autho-correlation አለመኖሩ ደግሞ በንጥል ድኅረት ትንተና የ"Durbin-Watson" ስልት ተፈትሾ (Auto-correlation ≈ 2) እሙኖቹ ተሟልተዋል። ከዚህ በተጨማሪም የመረጃዎቹ የልይይት መጠን እኩልነት (Homogeneity of variances) በሌቪን የልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ (Levene's Test of Equality of Variances) ተመርምሮ እሙኑ መሟላቱ የተረጋገጠ ($P > .05$) ሲሆን፣ የልይይት-አበር ልይይት ተመሳስሎ (Homogeneity of variance-covariance matrices) በቦክስ ኤም የአበር ልይይቶች ተመጣጣኝነት መፈተሻ ቴስት (Box's M)፣ የመረጃዎች ቀጥተኛ ተዛምዶ (Linearity) ደግሞ በብትን ክፋይ (scatterplot matrix) ተፈትሾ እሙኑን ያሟላ ሆኗል::

የውጤት ትንተና

ቀደም ብሎ በቀረበው የመረጃ አተናተን ክፍል እንደተገለጸው በማንበብ ምዘናዎች ከ160 የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከስምንት መምህራን ደግሞ በክፍል ውስጥ ምልከታና በሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የመምህራን ቁልፍ የማስተማር ተግባራት (ማቀድ፣ የክፍል አመራር፣ መመዘን) የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለውን አስተዋፆ ለመለየት ትንተናዎች ተካሄደዋል:: የመተንተኛ ስልቱ እሙኖች መሟላታቸው አስቀድሞ ከተረጋገጠ በኋላ፣ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄዎች አንጻር በጥንድ ተላውጦ ድኅረት የትንተና ስልት እየተሰሉ ቀርበዋል። ከዚያ በፊት ግን እያንዳንዱ ተንባይ ተላውጦ ከማንበብ አላባዎች ጋራ በተናጠል ያለው ተዛምዶ መሰላትና አስቀድሞ ተዛምዶ መኖሩ መረጋገጥ ስለሚኖርበት (Kiernan, 2014) ፍተሻው ተካሄዶ በሠንጠረዥ 1 የተመላከተው ውጤት ተገኝቷል።

ሠንጠረዥ 1

የመምህራን ቊልፍ የማስተማር ተግባራትና የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ዝምድና የፒርሰን ተዛምዶ (Pearson correlation) ውጤት

ተዛምዶ/Correlations									
	ማቀድ	የክፍል አመራር	መመዘን	1	2	3	4	5	6
የፊደል ስያሜ ዕውቀት (1)	.829*	.740*	.828*	1					
የንግግር ድምፆች ግንዛቤ (2)	.304	.794*	.608	.276**	1				
የተዘውታሪ ቃላት ንባብ (3)	.900**	.726*	.799*	.818**	.216**	1			
የፈጠራ ቃላት ንባብ (4)	.911**	.846	.715*	.861**	.241**	.853**	1		
አቀላጥፎ ማንበብ (5)	.946**	.737*	.826*	.761**	.235**	.869**	.836**	1	
አንብቦ መረዳት (6)	.721*	.718*	.714*	.277**	.130	.311**	.324**	.328**	1

Note. *. Indicates correlation is significant at the 0.05 level (2-tailed) while ** indicates correlation is significant at the 0.01 level (2-tailed).

በሠንጠረዥ 1 እንደተመላከተው ማቀድና መመዘን ከተማሪዎች የንግግር ድምፆች ግንዛቤ ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጒልህ ዝምድና የሌላቸው ($r < .7$, $P > .05$) ሲሆን በሌሎች የዝምድና ፍተሻዎች ግን ተንባይ ተላውጦዎች ከሁሉም ተተንባይ የማንበብ ችሎታ ተላውጦዎች ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጒልህ ተዛምዶ እንዳላቸው ($r > .7$, $P < .05$) ማረጋገጥ ተችሏል። ቀጥሎ የጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና ውጤቶች ቀርበዋል።

የጥናቱ የመጀመሪያ መሠረታዊ ጥያቄ "የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል አስተዋፆ አለውን?" የሚለው ነው:: 30 ነጥቦች ባሉት የማመሳከሪያ ቅፅ በመታገዝ በመምህራን ዕለታዊ የትምህርት እቅዶች አፈጻጸም ላይ በተካሄደ የሰነድ ፍተሻ የተገኙ መረጃዎችንና በምዘና የተሰበሰቡ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ መረጃዎች በድኅረት ትንተና ስልት ተሰልተው የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 2 ቀርበዋል።

በተጋርቶ መጠን "R2" ስሌት የተተንባዩ ተላውጦ ምን ያህል ልይይት በተንባዩ ተላውጦ ተገለጸ? የሚለውን የሚያመለክት ሲሆን የተገኘው ውጤት ወደመቶኛ ተሰልቶ ይገለጻል:: በዚህም ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ውጭ ባሉ የተማሪዎች የማንበብ ውጤት ላይ ከታየው ለውጥ ከ51.9% – 81.6% የሚሆነው በመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር ላይ የተገለጸ እንደሆነ የቀረበው መረጃ ያመላክታል:: መረጃው የመምህራን የእቅድ ትግበራ አፈጻጸም ከተማሪዎች የተዘውታሪና የትርጒምአልባ ቃላት፣ አቀላጥፎ የማንበብና የንግግር ድምፅ ግንዛቤ ችሎታ ጋራ ከፍተኛ ($R2 > .50$) ግንኙነት እንዳለውና በከፍተኛ ደረጃ ክሂሎቹን መተንበይ እንደቻለ ወይም የማቀድ ተግባር ቢሻሻል የተማሪዎች የማንበብ ውጤት እንዲሻሻል ሊያደረግ የሚችል መሆኑን ያረጋገጠ ሲሆን፣ ዕለታዊ የትምህርት እቅድ ማዘጋጀት የንግግር ድምፆች ግንዛቤን የመግለጽ/የመተንበይ አቅሙ አነሰተኛ መሆኑን ($R2 = 9.3\%$) አመላክቷል (Fernando, 2024)::

ሠንጠረዥ 2

የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር (planning practice) የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው አስተዋፆ የጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና (bivariate regression analysis) ውጤት

የምዘና ዓይነት	የተጋርቶ መጠን (R^2)	መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ *Beta* (β)	*F*	ትክክል የመሆን/የጉልህነት ደረጃ (sig.)
የፊደል ስያሜ ዕውቀት	.687	.829	13.184	.011
የተዘውታሪ ቃላት ንባብ	.811	.900	25.662	.002
የትርጉምአልባ ቃላት ንባብ	.831	.911	29.463	.002
አቀላጥፎ ማንበብ	.896	.946	51.466	.000
የንግግር ድምፆች ግንዛቤ	.093	.304	.612	.464
አንብቦ መረዳት	.519	.721	6.487	.044

Note. Df= (1,114)

የመደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (β) ስሌት ደግሞ ነጻ ተላውጦው በአንድ መደበኛ ልይይት ሲጨምር/ሲሻሻል በእያንዳንዱ ጥገኛ ተለውጦ ላይ በአማካይ ምን ያህል ለውጥ/መሻሻል ተስተዋለ? የሚለውን የሚገልጽ ነው:: በሠንጠረዥ 2 እንደተመለከተው የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር በአንድ መደበኛ ልይይት ሲለወጥ፣ ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ውጪ ባሉ የተማሪዎች የማንበብ ውጤት ላይ ከ.721 – .946 መደበኛ ልይይት ለውጥ ታይቷል:: ውጤቱ የመምህራን የማቀድ ተግባር አፈጻጸም ከተማሪዎች የፊደል ስያሜ፣ የተዘውታሪና የትርጉምአልባ ቃላት፣ አቀላጥፎ የማንበብና አንብቦ የመረዳት ውጤት ጋራ ከፍተኛ አዎንታዊ ተዛምዶ ያለው መሆኑንና ክሂሎቹን በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለ፣ (የመምህራን የማቀድ ተግባራት ከተሻሻሉ የተማሪዎቹ የማንበብ ችሎታ ሊሻሻል የሚችል መሆኑን) ($\beta >$ .50) ያመላከተ ሲሆን፣ ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ጋራ ያለው ተዛምዶ ግን አነስተኛ እንደሆነ (β= .304) እና ክሂሉን መተንበይ የቻለው በአነስተኛ ደረጃ እንደሆነ አሳይቷል (Nieminen, 2022)::

የተዛምዶ ደረጃውን አጠቃሎ የሚገልጸው ትክክል የመሆን/የጉልህነት ደረጃ ውጤቱም (significance level/*P*) የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር በንግግር ድምፆች ግንዛቤ ላይ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ እንደሌለውና ክሂሉን መተንበይ ያልቻለ መሆኑን ያመላከተ ሲሆን (*F* (1,114) = .612, *P*= .464)፣ ከፊደል ስያሜ ዕውቀት፣ ከተዘውታሪና ትርጉምአልባ ቃላት ንባብ፣ አቀላጥፎ ከማንበብና አንብቦ ከመረዳት ጋራ ያለው ተዛምዶ ግን ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ መሆኑንና ክሂሎቹን በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለና የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር ከተሻሻለ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ሊሻሻል እንደሚችል (P < .05) አረጋግጧል (የፊደል ስያሜ ዕውቀት *F* (1,114) = 13.184, *P* = .011)፣ የተዘውታሪ ቃላት ንባብ *F* (1,114) = 25.662, *P* = .002)፣ የትርጉምአልባ ቃላት ንባብ *F* (1,114) = 29.463, *P* = .002)፣ አቀላጥፎ የማንበብ *F* (1,114) = 51.466, *P* = .000)፣ አንብቦ የመረዳት *F* (1,114) = 6.487, *P* = .044)::

"የመምህራን የክፍል አመራር የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል አስተዋፆ አለውን?" የሚለው የጥናቱ ሁለተኛ መሠረታዊ ጥያቄ ነው:: ለጥያቄው ምላሽ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎች 20 ነጥቦች ባሉት የማመሳከሪያ ቅፅ በመመራት በተካሄደ የክፍል ውስጥ

ምልከታና በማንበብ ምዘናዎች ተሰብስበዋል፤ መረጃዎቹ በጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና ተሰልተው የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 3 ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 3

የመምህራን የክፍል አመራር (classroom management) የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያለው ሚና የጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና (bivariate regression analysis) ውጤት

የምዘናው ዓይነት	የተጋርቶ መጠን (R^2)	መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ Beta (β)	F	ትክክል የመሆን/የጕልህነት ደረጃ (sig.)
የፊደል ስያሜ ዕውቀት	.548	.740	7.269	.036
የተዘውታሪ ቃላት ንባብ	.527	.726	6.684	.041
የትርጉምአልባ ቃላት ንባብ	.517	.746	6.295	.034
አቀላጥፎ ማንበብ	.544	.737	7.146	.037
የንግግር ድምፆች ግንዛቤ	.630	.794	10.209	.019
አንብቦ መረዳት	.515	.718	6.375	.045

Note. Df= (1,114)

በሠንጠረዥ 3 እንደተመላከተው በተማሪዎች የማንበብ ውጤት ላይ ከታየው ለውጥ ከ51.5% – 63.3% የሚሆነው በመምህራን የክፍል አመራር ተግባር አፈጻጸም ላይ የተንጸባረቀ መሆኑን የቀረበው የተጋርቶ መጠን "R^2" ውጤት ያስረዳል:: የተገኘው ውጤት በክፍል አመራር ተግባራት አፈጻጸምና በተማሪዎች ውጤት መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ መኖሩንና የክፍል አመራር ተግባሩ የተማሪዎችን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለ (የክፍል አመራር ቢሻሻል የተማሪዎች ውጤት ሊሻሻል እንደሚችል) አመላክቷል (R^2 > .50) (Fernando, 2024):: የመደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ *(β)* ስሌት እንዳመለከተውም የመምህራን የክፍል አመራር ተግባር በአንድ መደበኛ ልይይት ሲጨምር/ሲሻሻል፣ በተማሪዎች የማንበብ ውጤት ላይ በአማካይ ከ.718 – .794 መደበኛ ልይይት ጭማሪ ታይቷል:: ይህም የመምህራን የክፍል አመራር ተግባር አፈጻጸም ከተማሪዎች ከሁሉም በአማርኛ ቋንቋ የማንበብ ችሎታዎች ጋራ ያለው ተዛምዶ ከፍተኛ መሆኑንና ክሂሎቹን መተንበይ መቻሉን (የክፍል አመራር አፈጻጸም ከተሻሻለ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ሊሻሻል የሚችል መሆኑን) (β > .50) ያመላከተ ሆኗል::

የድኅረት ትንተናው፣ የመምህራን የክፍል አመራር ከፊደል ስያሜ ዕውቀት ጋራ (F [1,114] = 7.269, P = .036)፣ ከተዘውታሪ ቃላት ንባብ ጋራ (F [1,114] = 6.684, P = .041)፣ ከትርጉምአልባ/የፈጠራ ቃላት ንባብ ጋራ (F (1,114) = 6.295, P = .034)፣ አቀላጥፎ ከማንበብ ጋራ (F [1,114] = 7.146, P = .037፣ ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ጋራ (F [1,114] = 10.209, P = .019)፣ እንዲሁም አንብቦ ከመረዳት ጋራ (F [1,114] = 6.375, P = .045) ትክክል የመሆን ደረጃ/ጕልህ ግንኙነት እንዳለውና ክሂሎቹን መተንበይ እንደቻለ አመላክቷል።

ሦስተኛው የጥናቱ መሠረታዊ ጥያቄ "የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ተግባር የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል አስተዋፆ አለውን?" የሚለው ነው:: 10 ነጥቦች ባሉት የማመሳከሪያ ቅፅ በተካሔደ ምልከታ የተገኙ የመምህራን የምዘና አፈጻጸምና በምዘና የተሰበሰቡ

የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ/ውጤት መረጃዎች በጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና ተሰልተው የተገኙ ውጤቶች በሠንጠረዥ 4 ቀርበዋል።

ሠንጠረዥ 4

የመምህራን የምዘና ተግባር (classroom assessment practice) የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሳደግ ያለው ሚና የጥንድ ተላውጦ ድኅረት ትንተና (bivariate regression analysis) ውጤት

የምዘናው ዓይነት	የተጋርቶ መጠን (R^2)	መደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ Beta (β)	*F*	ትክክል የመሆን/የጕልህነት ደረጃ (sig.)
የፊደል ስያሜ ዕውቀት	.685	.828	13.053	.011
የተዘውታሪ ቃላት ንባብ	.638	.799	10.585	.017
የትርጉምአልባ ቃላት ንባብ	.512	.715	6.288	.046
አቀላጥፎ ማንበብ	.682	.826	12.865	.012
የንግግር ድምፆች ግንዛቤ	.370	.608	3.526	.109
አንብቦ መረዳት	.510	.714	6.251	.047

Note. Df= (1,114)

በሠንጠረዥ 4 እንደተመላከተው በተማሪዎች ውጤት ላይ ከታየው ለውጥ ከ51.0% – 68.5% የሚሆነው በመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና አፈጻጸም ላይ የታየ መሆኑን (ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ በስተቀር) የቀረበው የተጋርቶ መጠን "R^2" ውጤት ያስረዳል:: ውጤቱ በመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ተግባራት አፈጻጸምና በተማሪዎች የማንበብ ውጤት መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ መኖሩንና የምዘና ተግባሩ የተማሪዎችን ውጤት በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለ (የምዘና አፈጻጸሙ ቢሻሻል የተማሪዎች ውጤት ሊሻሻል እንደሚችል) አመላክቷል (R^2 > .50) (Fernando, 2024):: የመደበኛ ድኅረታዊ መጣኝ (β) ስሌቱም የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ተግባር በአንድ መደበኛ ልይይት ሲጨምር/ሲሻሻል፣ በተማሪዎች የማንበብ ውጤት ላይ (ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ በስተቀር) በአማካይ ከ51.0 – 68.5 መደበኛ ልይይት ጭማሪ እንደታየ አረጋግጧል:: ይህም የመምህራን የክፍል ውስጥ የምዘና ተግባር አፈጻጸም ከተማሪዎች ከሁሉም የማንበብ ችሎታዎች ጋራ ያለው ተዛምዶ ከፍተኛ መሆኑንና ክሂሎቹን መተንበይ መቻሉን (የመምህራን የክፍል አመራር ተግባር አፈጻጸም ሲሻሻል የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ሊሻሻል የሚችል መሆኑን) (β > .50) አመላክቷል::

ትክክል የመሆን/ጕልህነት ስሌቱም (significance level/*P*)፣ የመምህራን የክፍል ውስጥ የምዘና አፈጻጸም ከተማሪዎች የፊደል ስያሜ ዕውቀት (F (1,114) = 13.053, P = .011)፣ የተዘውታሪ ቃላት ንባብ (F (1,114) = 10.585, P = .017)፣ የትርጉምአልባ/የፈጠራ ቃላት ንባብ (F (1,114) = 6.288, P = .046)፣ አቀላጥፎ የማንበብ F (1,114) = 12.865, P = .012) እና አንብቦ የመረዳት F (1,114) = 6.251, P = .047) ችሎታ ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጕልህ ተዛምዶ እንዳለው (P < .05) የድኅረት ትንተናው አመላክቷል:: ይህም የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና አፈጻጸም የተማሪዎችን የማንበብ ውጤት/ችሎታ በሚገባ መተንበይ እንደቻለ (የምዘና ተግባር ቢሻሻል የተማሪዎች የማንበብ ውጤት ሊሻሻል እንደሚችል ያመላከተ) ሆኗል:: በአንጻሩ የመምህራን የክፍል ውስጥ የምዘና ተግባር ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ጋራ

ያለው ተዛምዶ ግን ስታስቲካዊ ትክክል በመሆን ደረጃ/ጉልህ እንዳልሆነ የትንተናው ውጤት (F (1,114) = 3.526, P = .109) አሳይቷል::

የውጤት ማብራሪያ

በውጤት ትንተናው እንደተገለጸው የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር አፈጻጸም ከተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ጋራ አዎንታዊ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ እንዳለውና ክሂሉን በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለ የድኅረት ትንተና ውጤቱ አመላክቷል (β = .721 – .946, R^2 = .519 – .896, P <.05):: የተገኘው አዎንታዊ ውጤት ከChizhik and Chizhik (2018)፣ Janssen et al. (2019)፣ Karngbeae and Kennedy (2022) እና Lai and Lam (2011) ጸሕፍት ሐሳቦች ጋራ የተደጋገፈ ነው:: እንደጸሕፍቱ፣ ትምህርትን ማቀድ ከመምህራን ቀዳሚ ኃላፊነቶች መካከል ሲሆን ተግባሩ በዕውቀት የሚከወን ዋና ዓላማውም የትምህርቱን ዓላማዎች በማሳካት በተማሪዎች ላይ የአሠራርና የአስተሳሰብ ለውጥ ማምጣት ነው:: በዚህ የማቀድ ተግባር የግብ ጠቋሚ ዓላማዎች ይቀረጻሉ፤ ወደግብ አድራሽ ይዘቶችና ስልቶች (ሥነዘዴዎች) ይለያሉ፤ ማሳለጫ ግብዓቶች (መርጃ መሣሪያዎች) ይወሰናሉ፤ የግብ ስኬት ማረጋገጫ የምዘና ስልቶች ይቀርባሉ:: እነዚህ ዐበይት ጉዳዮች በወጉ ሲታቀዱ የእቅዱ ዓላማ (የተማሪዎችን ውጤት ማሻሻል) እውን ይሆናል:: በዚህ ጥናት በሁለቱ ተላውጦዎች መካከል (የመምህራን የትምህርት እቅድ ዝግጅትና የተማሪዎች የማንበብ ውጤት) የተመላከተው አዎንታዊ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶም፣ በጸሕፍቱ የተገለጹ ዝርዝር የእቅድ ጉዳዮች በወጉ ሲፈጸሙ እውን ሊሆን እንደሚችል የሚታመን ይሆናል:: በአንጻሩ ከንግግር ድምፅ ግንዛቤ ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ ያልተገኘው (β = .304, R^2 = .093, P = .464) የማቀድ ተግባራቱ በሚገባ ሳይከናወኑ በመቅረታቸው እንደሆነ ይታሰባል::

Farhang et al. (2023) እና Karngbeae and Kennedy (2022) ያካሄዷቸው ጥናቶችም የዚህን ጥናት አዎንታዊ ውጤት ደግፈዋል:: እንደጥናቶቹ፣ በጥናቱ ከተሳተፉ መምህራን መካከል ውጤታማ የሆኑት ተግባራትን ሳያንጠባጥቡ በማካተታቸው፣ ተግባራቱ በተሻለ ዘዴ የሚቀርቡበትን አቅጣጫ በመጠቆማቸው፣ ሙሉ ጊዜው ለትምህርቱ እንዲውል ለተግባራቱ ተገቢ የሰዓት ምደባ በማድረጋቸው፣ ተጠየቃዊ የየይዘት አቀራረብን በመፍጠር የመማር ዕድልን ሊያሰፉ የሚያስችል እቅድ በማዘጋጀታቸው፣ የእቅድ ተግባራቸው ከተማሪዎቻቸው ውጤት ጋራ ከፍተኛ ተዛምዶ ማሳየቱን ሲገልጹ፣ ትምህርትን ለማቀድ ዕውቀት የሚያንሳቸው መምህራን ግን የእቅድ አፈጻጸማቸው ከተማሪዎቻቸው ውጤት ጋራ ያለው ግንኙነት ከሚጠበቀው በእጅጉ ያነሰ ሆኗል:: በተመሳሳይ Enow and Goodwyn (2018)፣ Farhang et al. (2023)፣ König et al. (2021) እና Saad et al. (2010) በርእሰጉዳዩ ላይ ካካሄዷቸው ጥናቶች በመነሳት ባቀረቡት ማብራሪያ፣ ትምህርትን በወጉ ማቀድና በታለመው አግባብ መተግበር በተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ተነሳሽነት ላይ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፣ በንቃትና በትጋት የመማር ዕድልን ያሰፋል፣ የትምህርቱ ጊዜ ለታለመለት ዓላማ ብቻ እንዲውል ያስችላል፤ ክፍተቶችን እየለዩ ድጋፍ ለመስጠትና ዓላማው ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ ያስችላል፤ ሂደቱ የተማሪዎቹን ችሎታ በማሳደግ የሚያስመዘግቡትን ውጤት ከፍ ያደርጋል:: በዚህ ጥናት እንደተገኘው ጉልህ የተዛምዶ ውጤት የመምህራን ትምህርትን የማቀድ ተግባር ከተማሪዎች ውጤት ጋራ እንዲገናኝ ጊዜ ሰጥቶ፣ በዕውቀት በተመራ ሁኔታ ተግባሩን ማከናወን እንደሚገባ መረዳት ይቻላል::

በሌላ በኩል ደግሞ የመምህራን የክፍል አመራር ከተማሪዎቹ ከሁሉም የማንበብ ውጤቶች ጋራ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለውና የማንበብ ችሎታን በከፍተኛ ደረጃ መተንበይ እንደቻለ ከድኅረት ትንተናው የተገኘው ውጤት አረጋግጧል (β = .718 – .794, R^2 = .515 – .630, P <.05):: ይህ አዎንታዊና ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህነት ያለው ውጤት በተለያየ ዐውድ በበርካታ አካባቢዎች በተካሄዱ ጥናቶች የተደገፈ ነው:: Chibsa (2024) ባካሄዱት ጥናት በወጉ የተዘጋጀን እቅድ በክፍል ውስጥ በትክክል በመተግበር ለተማሪዎቻቸው አሳታፊ የመማር እድል የሚፈጥሩ መምህራን የተማሪዎቻቸውን ውጤት ማሻሻል እንደሚችሉ 72% መረጃ ሰጪዎች እንደሚምኑ ያሳየ ውጤት አቅርበዋል:: Wenglinsky (2002) ደግሞ የNAEP ዓለም አቀፍ የ15 ዓመት ተማሪዎችን ምዘና መሠረት በማድረግ በ7146 የ8ኛ ክፍል አሜሪካዊያን ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት የመምህራን የክፍል አመራር ተግባር አፈጻጸም ከተማሪዎች የትምህርት ውጤት ጋራ ከፍተኛ ግንኙነት እንዳለው አረጋግጠዋል:: Olayvar (2021) በበኩላቸው በመምህራን የክፍል አመራርና በተማሪዎች የእንግዝሊዝኛ ቋንቋ ውጤት መካከል ከፍተኛ ዝምድና እንዳለ (r = .853) በጥናታቸው በማረጋገጥ፣ አፈጻጸሙ እየተሻሻለና እየጠነከረ ቢሄድ የተማሪዎች ውጤትም አብሮ ሊሻሻል እንደሚችል በውጤት ማብራሪያው ላይ ገልጸዋል::

Thomas et al. (2010) እንዲሁ የተማሪዎች ውጤት በመምህራን የክፍል አመራር ተግባር ጥራት የሚወሰን ሲሆን የመምህራን ውጤት የሚለካው ደግሞ ተማሪዎች ባስመዘገቡት ውጤት እንደሆነ ገልጸዋል:: የመምህራን ዋና ኃላፊነት በክፍል ውስጥ ይፈጸማል፤ ኃላፊነቱ በታቀደው መሠረት የተማሪዎችን ዕውቀት፣ ክሂልና አመለካከት የሚለውጥ ትምህርት ማቅረብ ነው፤ ከክፍል ውጭ ያሉ የመምህራን ተግባራት ለክፍል ውስጥ አፈጻጸሞች ደጋፊ እንጂ ዋና አይደሉም፤ በመሆኑም ልዩ ትኩረት ሊሰጥ የሚገባው ለክፍል አመራር ሂደት ነው፤ በማለት ከጥናት ውጤታቸው በመነሳት የገለጹት ደግሞ Zhu and Kaiser (2022) ናቸው:: ባጠቃላይ የክፍል ውስጥ የመምህራን የክፍል አመራር በትምህርት እቅድና በዓላማ ስኬት ምዘና መካከል ያለ ድልድይ ሲሆን በጠቅላላ የመማር ማስተማር ሂደቱና (የተማሪዎች ችሎታ/ውጤት) እና የትምህርት ሥርዓት ውጤታማነት መገለጫ ዐቢይ ተግባር እንደሆነ በዚህ ጥናትና ዋቢ ተደርገው የቀረቡ ጥናቶች አመላክተዋል (Adeleke & Akere, 2023; Wenglinsky, 2001):: ከዚህ በተቃራኒ ግን ቀደም ሲል ከቀረቡና የክፍል አመራር በማንበብ ችሎታ ላይ አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለው ከገለጹ ጥናቶች የሚቃረን ጥናት በFarook and Ahmed (2021) ቀርቧል። ተመራማሪዎቹ 255 የ2ኛ ደረጃ ተማሪዎችን በማሳተፍ ባካሄዱት ጥናት፣ በመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችን በድኅረት ትንተና ስልት ተንትነው የክፍል አደረጃጀት ከተማሪዎች ውጤት ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ አዎንታዊ ዝምድና እንደሌለውና ውጤቱን መተንበይ እንዳልቻለ የሚያመለክት ውጤት (R^2 = .041, P = .514) አግኝተዋል:: ይህም ርእሰጉዳዩን በተጨማሪ ጥናቶች የመመርመር አስፈላጊነትን የሚጠቁም ነው።

የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ተግባር፣ የጀማሪ ክፍል ተማሪዎችን በአማርኛ የማንበብ ችሎታ የማሻሻል ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ በተመለከተም፣ በድኅረት ትንተናው የተገኘው ውጤት የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና አፈጻጸም ከንግግር ድምፆች ግንዛቤ ውጭ ካሉ የማንበብ ውጤቶች ጋራ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለውና ክሂሎቹን መተንበይ እንደቻለ አረጋግጧል (β = .714 – .828, R^2 = .510 – .685, P <.05):: Calonia et al. (2023) እንደሚሉት ከመማር ማስተማር ተግባራት መካከል ዐቢይ ቦታ የሚይዘው ምዘና፣ እቅድን ከውጤት ጋራ የሚያስተሳስር፣ የትምህርት ዓላማ እንዲሳካ ክፍተቶችን በማመላከት ማስተካከያ እንዲደረግ የሚያስችል፣ በምን ያህል

ደረጃ ውጤት እንደመጣ መረጃ የሚሰጥ እንደሆነ ሲገልጹ፣ Ullah et al. (2021) በበኩላቸው በተለይም ሂደታዊ የሆነው የክፍል ውስጥ ምዘና ለላቀ ውጤት ተነሳሽነትን የሚያሳደግ፣ መደጋገፍን የሚፈጥር ነው፤ ይላሉ:: ከጸሕፍቱ ሐሳብ ጋራ በተገናኘ በዚህ ጥናት የተገኘው አዎንታዊ የተዛምዶ ውጤትም፣ የእቅድና የክፍል አመራር ተግባራትን በማስተሳሰር፣ ክፍተቶችን ማመላከት በመቻል፣ የውጤት ደረጃን በማሳየት፣መደጋገፍ እንዲኖር በማድረግ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል::

ከጸሕፍት ሐሳብ በተጨማሪ የጥናቱ ውጤት ከተለያዩ የጥናት ውጤቶች ጋራም እንዲሁ ተደጋግፏል:: በጆርጂያ ስቴት ዩንቨርሲቲ መምህር የሆኑት Li (2012) ከዓለም አቀፉ የ15 ዓመት ተማሪዎች የ2009 ምዘና (PISA) ወጤት የአሜሪካን ተማሪዎች ነጥለው በመውሰድ ባካሄዱት ጥናት በሂደታዊ ምዘናዎች (formative assessment) እና በተማሪዎች የማንበብ ውጤት መካከል ከፍተኛ ተዛምዶ እንዳለና ምዘናው ከተማሪዎች የማንበብ ፍላጎት ጋራ ዝምድና እንዳለው፣ የመምህር-ተማሪ ግንኙነቶችንም በአዎንታዊነት እንደሚያሻሽልም አሳይተዋል:: በተመሳሳይ Xuan et al. (2022) ባጠቃላይ 116,051 ተማሪዎችን በማሳተፍ የተካሄዱ 48 መጠናዊ ጥናቶች ላይ ልዕለትንተና አድርገው ሂደታዊ የክፍል ውስጥ ምዘና ከተማሪዎች የማንበብ ውጤት ጋራ አዎንታዊ መካከለኛ ግንኙነት (ES = +0.19) እንዳለው አመላክተዋል:: Yan and Chiu (2021) በበኩላቸው የ19 ሀገሮች 151,969 የ15 ዓመት ዕድሜ ተማሪዎችን ባካተተው የPISA 2018 ጥናት ላይ በመመሥረት ባካሄዱት ጥናት፣ ግቦችን ግልጽ በማድረግና መሻሻሎችን በመመዘን በሚገኘው ውጤት ላይ በመመሥረት የሚደረግ የመማር ማስተማር ሂደት ከተማሪዎች የማንበብ ውጤት ጋራ አዎንታዊ ተዛምዶ እንዳለው አረጋግጠዋል:: በዚህ ጥናትም፣ የምዘና ሂደት የመምህር-ተማሪ ግንኙነቶችን ሲያሻሽል፣ ግቦችን ግልጽ ሲያደርግና መሻሻሎችን በመከታተል ክፍተቶችን መሙላት ሲያስችል የመምህራን የክፍል ውስጥ ምዘና ከተማሪዎች የማንበብ ውጤት ጋራ አዎንታዊ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ እንደሚኖረው መረዳት ይቻላል:: የCai et al. (2022) ጥናት ውጤት ግን እስካሁን ከቀረበው ተቃራኒ ሆኗል። አጥኚው 4837 የሆንግኮንግ ተማሪዎችን በማሳተፍ ባካሄዱት ጥናት ያሰባሰቧቸውን መረጃዎች በመዋቅራዊ ስሌት ሞዴል ተንትነው፣ ሂደታዊ ምዘና በዝቅተኛና በመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ አዎንታዊ ተጽእኖ እንዳለው፣ በከፍተኛ ደረጃ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ ግን ያሳደረው ተጽእኖ ስታቲስቲክሳዊ አለመሆኑን የሚያመለክት የጥናት ውጤት አቅርበዋል። ይህም ምዘና ከፍ ያለ ችሎታ ባላቸው ተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ላይ አወንታዊ አስተዋፆ ያላሳደረው ለምን እንደሆነ በተጨማሪ ጥናቶች የመመርመር አስፈላጊነትን ይጠቁማል።

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት በምዘና፣ በምልከታና በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች በድኅረት ትንተና ስልት ተተንትነው የመምህራን ቊልፍ የማስተማር ተግባራት (ማቀድ፣ የክፍል አመራርና ምዘና) የቀዳማይ ክፍል ደረጃ ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል አዎንታዊ አስተዋፆ ያላቸው መሆኑንና ክሂሉን መተንበይ እንደቻሉ የሚያረጋግጡ ውጤቶች ተገኝተዋል። ውጤቶቹም በተለያዩ ጊዜያትና ዐውዶች ከተሠሩ በርካታ ጥናቶች ውጤቶች ጋራ ተደጋጋፊ ሆነዋል። ከዚህም የተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል የመምህራንን የዕውቀትና የአፈጻጸም ክሂል በማሳደግ የማቀድ፣ የአመራርና የምዘና ተግባራት በተሻለ ሁኔታ እንዲከናወኑ ማድረግ እንደሚገባ መገንዘብ ይቻላል። በማቀድ፣ በክፍል አመራርና በመመዘን አስተዋፆ ላይ ተቃራኒ የጥናት ውጤቶች መታየታቸው ደግሞ ተጨማሪ ምርምሮችን በማካሄድ የተላውጦዎቹን አስተዋፆ በበለጠ ማረጋገጥ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዘበ ሆኗል።

ማጠቃለያ

የመምህራን ቁልፍ የማስተማር ተግባራት የቀዳማይ ክፍል ደረጃ ተማሪዎችን የማንበብ ችሎታ ለማሻሻል ያላቸውን አስተዋፆ መመርመር የጥናቱ ዋና ዓላማ ነበር። የዚህን ገላጭ-ተዛምዷዊ ጥናት ሦስት መሠረታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ከ160 የ2ኛና የ3ኛ ክፍል ተማሪዎች በምዘና፣ ከ8 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ እንዲሁም በሰነድ ፍተሻ የተሰበሰቡ መረጃዎች በጥንድ ተላውጦ ድኅረት የትንተና ስልት ተፈትሸዋል። ከትንተናው በፊት ስልቱ የሚጠይቃቸው እሙኖች መሟላታቸው ተረጋግጧል። ከድኅረት ትንተናው የተገኙ ውጤቶችም የመምህራን ቁልፍ የማስተማር ተግባራት (ማቀድ፣ የክፍል አመራር፣ መመዘን) ከተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ጋራ (ከፊደል ስያሜ ዕውቀት፣ ከተዘውታሪና ትርጉምአልባ ቃላት ንባብ፣ አቀላጥፎ ከማንበብና አንብቦ ከመረዳት ጋራ) አዎንታዊ ትክክል የመሆን ደረጃ/ጉልህ ተዛምዶ እንዳላቸውና እነዚህ ቁልፍ የማስተማር ተግባራት ቢሻሻሉ የተማሪዎች የማንበብ ችሎታ ሊሻሻል እንደሚችል መተንበይ እንደቻሉ አረጋግጠዋል::

የተገኙ አወንታዊ ውጤቶች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የታየውን የጀማሪ ክፍል ተማሪዎች የማንበብ ውጤት ማሽቆልቆል ለመግታትና ለማሻሻል፣ መምህራን የትምህርት እቅዶችን ሲያዘጋጁ፣ ክፍል ሲመሩና ምዘና ሲያከናውኑ የሚታዩባቸውን የዕውቀትና የክሂል ውስንነቶችን በመለየት፣ በተከታታይ ሥልጠናዎች (ለምሳሌ፣ በትምህርት ጥናት፣ በተከታታይ የሙያ ማሻሻያ፣ በጉድኝት ወዘተ) ውስንነቶቹን በመሙላት፣ ተግባሮቹ (ማቀድ፣ መምራትና መመዘን) በማንበብ ችሎታ መዳበር ላይ አወንታዊ አስተዋፆ እንዲያበረክቱ ማድረግ የሚገባ መሆኑን የጠቆሙ ናቸው። ይህ እንዲሆን ደግሞ በተለይም መምህራንን የመደገፍና የማብቃት ኃላፊነት ያለባቸው የጉድኝት ሱፐርቫይዘሮችና ርእሳነመምህራን ድርሻቸው የጎላ ይሆናል። ከዚህ ሌላ ጥናቱ በ4 ትምህርትቤቶች፣ 160 ተማሪዎችንና 8 መምህራንን በማሳተፍ የተካሄደ መሆኑ የተገኙ ውጤቶችን የማጠቃለል አቅም ውስን እንደሚያደርገው ይታመናል። ይህም ሰፋ ባለ አካላይና የናሙና መጠን ተጨማሪ ጥናት የማካሄድ አስፈላጊነትን የሚጠቁም ነው።

ዋቢዎች

Adeleke, T., E., & Akere, O. M. (2023). Teacher classroom practices and academic performance of secondary school students in akinyele local government area of Oyo State, badan, Nigeria. *Journal of research & method in education (IOSR-JRME),13*(02), 44-49. https://www.academia.edu/112951449/

Ahmed, M. (2022). *Lesson plan evaluation template.* Pakistan international school, Jeddah. https://www.scribd.com/document/604077003/Lesson-Plan-Evaluation-Template

A'yunin, Q. (2020). *The effectiveness of question answer relationship (QAR) strategy to students' reading comprehension (A Pre Experimental Study in the Seventh Grade of SMPN 2 Ponorogo in Academic Year 2019/2020)* [Undergraduate (S1) thesis]. English education department, the state institute of Islamic studies, Ponorogo. https://etheses.iainponorogo.ac.id/8941/

Bandura, A. (1977). *Social Learning Theory.* Prentice-Hall.

Bas, G. (2025). *Factors related to instructional practices of teachers: Evidence from TALIS 2018.* The Asia-Pacifc education researcher, Singapore. https://doi.org/10.1007/s40299-025-01009-6

Beaulieu, R. (2023). *25 Best classroom management strategies every teacher should use.* Schools That Lead, USA. https://www.schoolsthatlead.org/blog/best-classroom-management-strategies

Bibon, M. B. (2022). Teachers' instructional practices and learners' academic achievement in science. *Contemporary Mathematics and Science Education, 3*(1), 1 – 14. Department of education, Albay, The Philippines. https://doi.org/10.30935/conmaths/11816

Bower, L. J. (2017). *Visual phonics: its impact as an instructional tool to promote literacy development in kindergarten students* [Graduate research paper]. University of Northern Iowa. https://scholarworks.uni.edu/grp/590

Cai, Y., Yang, M., & Yao, J. (2022). *More is not always better: the nonlinear relationship between formative assessment strategies and reading achievement.* Informa UK Limited, trading as Taylor & Francis Group. https://www.suibe.edu.cn/_upload/article/files/8d/eb/d81bf1404f99b92c7f76a23d27dc/b6162f04-c071-4c68-ad93-262d3093456c.pdf

Calonia, J. T., Lopez, J. S., Bejoc, J. B., Malacad, R., Oro, D., & Cuesta, S. (2023). Teachers' instructional practices and students' academic achievement in a virtual learning environment. *International journal of innovative science and research technology, 8*(6), 489 – 495. https://doi.org/10.5281/zenodo.8115949

Cardenas, E. (2024). *Reading in the digital age: Engaging lifelong learning.* LinkedIn, Sunnyvale, California, USA. https://www.linkedin.com/pulse/reading-digital-age-engaging-lifelong-learning-cardenas-cphr-rnn8c

Castles, A., Rastle, K., & Nation, K. (2018). Ending the reading wars: Reading acquisition from novice to expert. *Psychological Science in the Public Interest, 19*(1), 5 –51. SAGE. https://psycnet.apa.org/doi/10.1177/1529100618772271

Chizhik, E. W., & Chizhik, A. (2018) Using activity theory to examine how teachers' lesson plans meet students' learning needs. *The teacher educator*, *53*(1), 67-85. San Diego State University.Routledge. https://www.researchgate.net/publication/322941737

Cox, J. (2024). *Explaining the 5 pillars of reading.* Teach Hub. https://www.teachhub.com/teaching-strategies/2024/05/explaining-the-5-pillars-of-reading/

EAES/Educational Assessment and Examinations Service. (April, 2022). *Early grade reading assessment (EGRA 2021) report.* Ministry of education, Addis Ababa.

Echevarría, J., Vogt, M. E., & Short, D. (2017). *Making content comprehensible for English learners: The SIOP Model* (5th ed.). Pearson.

Eekhof, L. S., Krieken, K. V., Sanders, J. & Willems, R. M. (2021). *Reading minds, reading stories: Social-cognitive abilities affect the linguistic processing of narrative viewpoint.* Frontiers Media SA, Lausanne, Switzerland. https://doi.org/10.3389/fpsyg.2021.698986

Enow, L., & Goodwyn, A. (2018). The invisible plan: how English teachers develop their expertise and the special place of adapting the skills of lesson planning. *English in Education*, *52*(2), 1-15. https://doi.org/10.1080/04250494.2018.1438119

Farhang, Q., Hashemi, S., & Ghorianfar, M. (2023). Lesson plan and its importance in teaching process. *International journal of current science research and review, 06*(08), 5901 – 5913. https://doi.org/10.47191/ijcsrr/V6-i8-57

Farook, M., & Ahmed, R. (2021). Classroom management practices and learners' academic achievement in public secondary schools in Rubaga division, Kampala-Uganda. *International Journal of Leadership Studies: Theory and Practice, 4*(3), 163-178. https://doi.org/10.52848/ijls.892827

Fernando, J. (2024). *R-Squared: definition, calculation, and interpretation.* The investopedia express podcast. https://www.investopedia.com/terms/r/r-squared.asp

Francisco, C.D.C., & Celon, L.C. (2020). Teachers' instructional practices and its effects on students' academic performance. *International journal of scientific research in multidisciplinary studies, 6*(7), 64 – 71. Malolos City, Bulacan, Philippines. https://files.eric.ed.gov/fulltext/ED607985.pdf

George, S. (2023). Five pillars of reading. *Information Matters, 3*(9). Asist, Delhi. https://informationmatters.org/2023/09/five-pillars-of-reading/

Goldberg, M. (2025). *Reading instruction at your child's school.* WETA, Washington, D.C. https://www.readingrockets.org/literacy-home/reading-101-guide-parents/reading-instruction-your-childs-school

Gump, H. M. (2024). *Teacher preparation and perceptions on readiness to address the science of reading* [Master's thesis]. Graduate School, University of Tennessee. https://trace.tennessee.edu/utk_gradthes/11381

Hogenboom, M. (2022). *What is the best age to learn to read?* https://melissahogenboom.substack.com/p/what-is-the-best-age-to-learn-to

Janssen, N., Knoef, M., & Lazonder, A. (2019). Technological and pedagogical support for pre-service teachers' lesson planning. *Technology Pedagogy and Education*, *28*(1), 1-14. https://doi.org/10.1080/1475939X.2019.1569554

Karngbeae, L. D. & Kennedy, G. M. (2022). Instructional planning: Its importance and basic components. *International journal of social science and education research studies, 02*(12), 802-810. https://doi.org/10.55677/ijssers/V02I12Y2022-13

Kern, M. L., & Friedman, H. S. (2009). Early educational milestones as predictors of lifelong academic
achievement, midlife adjustment, and longevity. *Journal of Applied Developmental Psychology*. *30*(4), 419–430. https://doi.org/10.1016/j.appdev.2008.12.025

Kiernan, D. (2014). *Correlation and simple linear regression.* Natural Resources Biometrics. https://milnepublishing.geneseo.edu/natural-resources-biometrics/chapter/chapter-7-correlation-and-simple-linear-regression/

König, J., Krepf, M., Bremerich-Vos, A., & Buchholtz, C. (2021). Meeting cognitive demands of lesson planning: introducing the CODE-PLAN model to describe and analyze teachers' planning competence. *The teacher educator*, *56*(4), 466–487. https://doi.org/10.1080/08878730.2021.1938324

Lai, E., & Lam, C. C. (2011). Learning to teach in a context of education reform: Liberal studies student teachers' decision-making in lesson planning. *Journal of Education for Teaching, 37*(2), 219–236. https://doi.org/10.1080/02607476.2011.558287

Li, H. (2012). *How is Formative Assessment Related to Students' Reading Achievement? Findings from PISA 2009.* Department of educational policy studies college of education and human development, Georgia State University. https://www.researchgate.net/publication/289527253

Li, S. (2015). *Early reading: Benefits of starting early*. Nature for the Future. https://nurtureforthefuture.wordpress.com/2015/01/31/early-reading-the-benefits-of-starting-early/

Lim, H. (2015). Social modeling effects on perception of the police. *Policing: An International Journal of Police Strategies & Management, 38*(4), 675–689. https://doi.org/10.1108/PIJPSM-02-2015-0018

Lin, C-H. (2001). *ERIC clearing house on reading English and communication bloomington in early literacy instruction.* ERIC Digest. https://files.eric.ed.gov/fulltext/ED459424.pdf

Ma, L., & Zhao, Z. (2025). Reading motivation and reading comprehension achievement among English majors in China: A descriptive correlational study. *Heylion, 11*(3), 1 – 10. https://doi.org/10.1016/j.heliyon.2025.e42427

NEAEA. (2013). *Ethiopian 4th national learning assessment of grades 4 and 8 pupils' data analytic report*. FDRE Ministry of Education. http://213.55.101.25/images/sirna_bar/Grade_4__8_NLA_Repots_2012.pdf

Nieminen, P. (2022). Application of Standardized Regression Coefficient in Meta-Analysis. *Biomedinformatics, 2*(3), 434–458. https://doi.org/10.3390/biomedinformatics2030028

NRP/National reading Panel. (2000). *Teaching children to read: An evidence-based assessment of the scientific research literature on reading and its implications for reading instruction*. National Institute of Child Health and Human Development.

Olayvar, S. R. (2021). Relationship between teachers' instructional practice and students academc performance in English during COVID-19 pandemic. *International journal of academic multidiciplinary research (LJAMR), 5*(7), 137 – 141. https://philpapers.org/archive/OLARBT.pdf

Osborne, M. C. (2021). Teacher instructional practices and student mathematics achievement. *Journal of educational research and practice, 11*(1), 345–358. https://doi.org/10.5590/JERAP.2021.11.1.25

Ozdemir, N. (2020). How to improve teachers' instructional practices: The role of professional learning activities, classroom observation and leadership content knowledge in Turkey. *Journal of Educational Administration*, *58* (6): 585–603. https://doi.org/10.1108/JEA-10-2019-0189

Palad, J. G. (2025). *Teacher classroom observation rating checklist.* https://www.scribd.com/document/627612364/

Piper, B. (2010). Ethiopia early grade reading assessment data analytic report: Language and early learning. *Prepared for USAID/Ethiopia under the education data for decision making.* (Ed Data II project), Task Number 7 and Ed Data II Task Number 9, research Triangle Park. NC: RTI International. http://213.55.101.25/images/sirna_bar/EGRA_2010.pdf

RAES. (2018). *Reading after epilepsy surgery: An introductory series for parents and educators.* Los Angeles, California. http://www.brainrecoveryproject.org/wp-content/uploads/2018/10/Part-1-Understanding-the-Big-Five-for-the-Early-or-Struggling-Reader.pdf

Rayner, K, Foorman, B. R., Perfetti, C. A, Pesetsky, D., & Seidenberg, M. S. (2001). How psychological science informs the teaching of reading. *Psychological science in the public interest, 2*(2), 31-74. https://www.jstor.org/stable/40062357

READ M&E. (2018). *Reading for Ethiopia's Achievement Developed Monitoring and Evaluation Early grade reading assessment (EGRA) 2018 endline report.* USAID. http://213.55.101.25/images/sirna_bar/EGRA_2018_Report_Draft_1_18-10-311.pdf

RTI International. (2016). *Early Grade Reading Assessment (EGRA) Toolkit*, (Second Edition). Washington, DC: United States Agency for International Development. https://ierc-publicfiles.s3.amazonaws.com/public/resources/EGRA%20Toolkit%20V2%202016.pdf

Saad, A., Chung, P., & Dawson, C. (2010). *The developmente of lesson planning system based on casebased reasoning (CBR) concept: The methodology.* Loughborough University. https://www.researchgate.net/publication/299466565

Terada, Y. (2019). *8 proactive classroom management tips: New teachers—and experienced ones too—can find ideas here on how to stop disruptive behavior before it begins.* George Lucas Educational Foundation. https://www.edutopia.org/article/8-proactive-classroom-management-tips/

Thomas, J. K., Eric, S. T., John, H. T., & Amy, L. W. (2010). *Identifying effective classroom practices using student achievement data.* National bureau of economic research, Massachusetts. https://www.nber.org/system/files/working_papers/w15803/w15803.pdf

Ullah, Z., Saba, N., Imran, S., Abouzar, M., Fazil, M., & Daraz, S. (2021). *An examination of teachers' instructional practices fostering student's engagement.* Department of education: Abdul Wali Khan University Mardan Pakistan. https://www.researchgate.net/publication/371753383

Untailawan, F. (2020). Improving students' reading comprehension and critical thinking skills through the implementation of QAR strategy at SMA PGRI Dobo. *Journal of social sciences and humanities, 10*(1), 93-103. Jalan Dolong, Halong Atas, Ambon-97231, Indonesia. https://www.researchgate.net/publication/341404422

Usher, E. L., & Schunk, D. H. (2018). Social cognitive theoretical perspective of self-regulation. In D. H. Schunk, and J. A. Greene (Eds.), *Handbook of self-regulation of learning and performance (2nd ed.)*, 19–35. New York: Routledge.

Wenglinsky, H. (2001). *Teacher classroom practices and student performance: How schools can make a difference.* Educational testing service, Princeton University. https://onlinelibrary.wiley.com/doi/pdf/10.1002/j.2333-8504.2001.tb01861.x

Wenglinsky, H. (2002, February 13). How schools matter: The link between teacher classroom practices and student academic performance. *Education policy analysis archives, 10*(12), 1 – 30. College of Education, Arizona State University. https://www.researchgate.net/publication/49610089

Widodo, A. & Astuti, B. (2024). Critical Analysis of Social Cognitive Learning Theory and Its Implementation in Elementary Schools. *MANDALIKA: Journal of Social Science*, (1), 6–12. https://doi.org/10.56566/mandalika.v2i1.148

Xuan, Q., Cheung, A., & Sun, D. (2022). The effectiveness of formative assessment for enhancing reading achievement in K-12 classrooms: A meta-analysis. *Front. Psychol. 13:990196.* https://doi.org/10.3389/fpsyg.2022.990196

Yan, Z., & Chiu, M. M. (2023). The relationship between formative assessment and reading achievement: A multilevel analysis of students in 19 countries/regions. *British Educational Research Journal*, *49,* 186–208. https://doi.org/10.1002/berj.3837

Yilmaz, U., & Yılmaz, M. (2019). The Relation Between Social Learning and Visual Culture. *International Electronic Journal of Elementary Education*, *11*(4), 421–427. https://doi.org/10.26822/iejee.2019450837

Zebron, M. (2022). *The Importance of Reading in Primary School.* British International School Phuket. https://www.bisphuket.ac.th/the-importance-of-reading-in-primary-school/

Zhu, Y., & Kaiser, G. (2022). Impacts of classroom teaching practices on students' mathematics learning interest, mathematics self-efficacy and mathematics test chievements: a secondary analysis of shanghai data from the international video study Global Teaching InSights. *ZDM Mathematics Education*, *54,* 581–593. https://doi.org/10.1007/s11858-022-01343-9